የፖለቲካ ምኅዳሩ ከፊት ማለቱ ተቃዋሚዎች በሕዝቡ ዘንድ ሰፊ የምርጫ ቅስቀሳ እንዲያካሂዱም ረድቷቸው ነበር። ቅስቀሳው ይበልጥ የተኪያሄደው በከተሞች ቢሆንም በገጠር ነዋሪውም ላይ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር። በድምጽ ማጉያ መሣሪያዎች፣ በበራሪ ጽሑፎች፣ በሬድዮና በቴሌቪዥን የተላለፉት መልእክቶች ለሕዝቡ ደርሰው ነበር። በተለይ በትላልቅ ከተሞች ኢሕአዴግና ተቃዋሚዎች በቅስቀሳ አንገት ላንገት የተናነቁበት ነበር። ቅስቀሳው ሊጠቃለል እስኪቃረብ ድረስም ጨዋነት በተሞላበትና በተረጋጋ ሁኔታ ተኪያሂዶ ኢሕአዴግ ሊቀለብሰው ወደማይችለው ደረጃ ደርሶ ነበር።

## *5.2 የመስቀል አደባባይ ሰልፎች*

የምርጫው ቅስቀሳ ሊጠቃለል ጥቂት ሲቀረው ከፍተኛ የኃይል ማሳያ ትዕይንት በመስቀል አደባባይ ተደርጎ፣ ተቃዋሚዎች መስቀል አደባባይ ላይ ሁለት ከፍተኛ ሰልፎችን ሲያኪያሂዱ፣ ኢሕአዴግም አንድ ከፍተኛና አንድ መለስተኛ ሰልፎችን አኪያሂዶ ነበር። በተቃዋሚዎች ከተጠሩት ሰልፎች በአንዱ ላይ እኔም በእንግድነት ተገኝቼ ነበር። የተገኘሁበት ሰልፍ ርእሰ ጉዳይ የኢሕአዴግ መንግሥት ሉዓላዊ መሬታችንን ለኤርትራ አሳልፎ ሰጥቷል የሚል ስለነበር ሰልፉ በተቃዋሚዎች ይዘጋጅ እንጂ ጉዳዩ አፈንጋጮች የተባልነውንም በቀጥታ የሚመለከት ነበር። በመሆኑም አዘጋጆቹ በሰልፉ ንግግር እንድናደርግ እኛንና ዶክተር ነጋሶን ሲጋብዙን በሰልፉ እንካፈል ወይስ አንካፈል በሚል የተወሰነ ውይይት አደረግን። በውይይቱ እንካፈል ካልን ገና ያላወቅነውን የተቃዋሚ ጎራ የደገፍን ልንመስል እንችላለን፤ አንሳተፍ ካልን ደግሞ ጉዳያችን የሆነውንና በነመለስ ሸር የተዳፈነውን አቋማችንን ለሕዝብ ሳንገልጽ እንቀራለን ተባብለን በመጨረሻ በሰልፉ መገኘቱን መረጥን።

በዚህ መሠረትም ዓለም ሰገድ ገብረአምላክ፣ አውዓሎም ወልዱ፣ የውብማር አስፋውና ገብሩ አሥራት በስብሰባው ተገኘን። በዚህ አጋጣሚም ሕዝቡ ቢያውቀው ይበጃል ያልኩትን የነመለስን ክሕደትና የኛን ስሕተት በጽሑፍ አቀረብኩ። በዚህ ስብሰባ፤ 1ኛ/ የአልጄርሱ ስምምነት ሲፈረም፣ 2ኛ/ ኤርትራ ነጻ ስትወጣ የኢትዮጵያን ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያን የዓሰብ ወደብ ባለቤትነት መብት ባለማስጠበቅ ተሳታፊ የነበርኩበት ኢሕአዴግ ለፈጸመው ታሪካዊ ስሕተት ሕዝቡን ይቅርታ ጠይቂያለሁ። የንግግሬን ሙሉ ቃል፤ *«ሻዕቢያ ነፍስ እንዲዘራ ያደረጉት አቶ መለስ ናቸው»*[18] በሚል ርእስ በጊዜው የነበረው ኢትኦጵ የተባለው የግል ጋዜጣ ዘግቦት ነበር። ከዶክተር ነጋሶጋ ምንም ሳንነጋገርና ሳንመካከር በስብሰባው ብንገኝም እንደ አጋጣሚ እርሱም የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቆ ነበር።

በዚህ በመስቀል አደባባይ ባደረኩት ንግግር ከፍተኛ የመንፈስ እርካታ አግኝቼበታለሁ። በአንድ በኩል፤ አፈንጋጮች የተባልነው በድርጅቱ በነበርንበት ጊዜ ከቀሩት የአመራር አባላት ጋ ስናራምደው የነበረውን የኢትዮጵያን ጥቅም ያላስጠበቀውንና ለኤርትራ ያደላውን አቋማችንን ለሕዝብ በይፋ ገልጸን ይቅርታ አለመጠየቃችንና ድርጅቱን ከለቀቅን በኋላም የእነ መለስን የኖርማላይዘሽንና የሰጥቶ መቀበል መርሕ አለማጋለጣችን በጣም ይቆጨን ነበር። ስለዚህ ያለፈውን ስሕተታችንንና የነመለስን ቀጣይ ጥፋት በአደባባይ ለመግለጽ በመቻሌ እጅጉን ተደስቼ ነበር። በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ የተገኘሁበት ዋና ምክንያት የኢሕአዴግን ጥፋት ለማጋለጥና ለመቃወም ቢሆንም ኢሕአዴግ በለመደው የእምዬን ወደ አብዬ ስልቱ ጉዳዩን አጣሞ፤ *«ገብሩ የታገለለትን ዓላማ ክዶ፤ በመታገሉም ተጸጽቶ*

[18] ኢትኦጵ፣ ረቡዕ ታኅሣሥ 27 ቀን 1997 ዓ.ም.፣ ገጽ 8

*ትምክሕተኞች ጫማ ላይ ወድቆ ይቅርታ ጠይቋል፤ ለትምክሕተኞች ተንበርክኳል፤»* የሚል አሉባልታ በስፋት ያሰራጭ ነበር። የኢሕአዴግ አመራር የራሱን ክሕደት ለመሸፈን ከትምክሕተኞችጋ ቢያሰልፈኝም ዋናው አጀንዳ ይኸ እንዳልነበር ግን ኢሕአዴግም፤ ሌሎቻችን እናውቅ ነበር። ለማንኛውም፤ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ አድርጎ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ተሠውተው ያስመለሱትን ባድመን ለሻዕቢያ አሳልፎ ከመስጠት የከፋ ክሕደትና ተንበርካኪነት የለምና፤ እኔንና ጓዶቼን በትምክሕተኝነት መክሰስና ሀልውናችንን የሚገልጸውን የትግል ታሪካችንን ለመደምሰስ መሞከሩ ሰሚ ያጣ ጩኸት ነበር።

ኢሕአዴግ በምርጫው ወቅት በሚድያ ያስተላልፋቸው የነበሩት ክርክሮች ዋጋ ቢስ እንደነበሩ በሚገባ ተገንዝቦ ነበር። በተለይ የአዲስ አበባ ሕዝብ መስቀል አደባባይ ወጥቶ የኢሕአዴግን የአገር ክሕደት ሲያወግዝ ይበልጡኑ ተደናግጦ ዐጸፋ ለመስጠት የሞከረው የፖለቲካ አቅጣጫውን ትክክለኝነት ለሕዝቡ በማስገንዘብ ሳይሆን *«ትምክሕተኞች ሊውጡህ ነው፤ ሊጨርሱህ ነው፤»* የሚለውን መፈክር በማስተጋባት ነበር። ይህን መፈክር በተለይ የትግራይንና የአንዳንድ ብሔረሰቦችን ሥነ-ልቦና ለመግዛት ተጠቅሞበት ነበር። በአጠቃላይ ይህ የኢሕአዴግ አኪያሄድ በፖለቲካ አቋሙ የተሸነፈ ማንኛውም ፓርቲ ስድቦችን፣ ውሸቶችንና አሉባልታዎችን በመንዛት ሕዝቡን በፍርሀትና በድንጋጤ ለማሸበር እንደሚሞክር አሳየ።

የምርጫው ቅስቀሳ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ወቅት ኢሕአዴግ የከፈተው ቀዳዳ ለሽንፈቱና ለውድቀቱ እንደዳረገው ሲረዳ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን ጠፍቶት አጥቶ ነበር። በተለይ በአዲስ አበባ የታየው የሕዝቡ እንቅስቃሴ ዕንቅልፍ ነስቶት ገንዘቡን እየበተነ የኢሕአዴግ የንብ ምልክት የነበሩባቸው ፖስተሮች፣ በራሪ ፓንፍሌቶች፣ ቲ ሸርቶችንና ሌሎች የቅስቀሳ ቁሳቁሶችን በማደል አዲስ አበባን አጥለቅልቋት ነበር። ቁጥር ስፍር የሌላቸው የመንግሥት መኪኖችን በማሳማራትም ከተማውን በድምጽ አውከት ነበር። ሆኖም በሕዝቡ ኅሊና የተቀረጸው የኢሕአዴግ አመራር ምስል የአገር ጥፋት፣ በሙስና የመዘፈቅ፣ የብልሹ አስተዳደርና የፈላጭ ቆራጭነት መንሰራፋት ነበርና ይህ ሁሉ ግርግር ሕዝቡ ልብ ውስጥ ሊገባ አልቻለም ነበር። በዚህ ሁኔታ እጅግ የተበሳጨው ኢሕአዴግ የሕዝቡ ከፍተኛ ድጋፍ እንዳለው ለማሳየት በአዲስ አበባ ሁለት ትዕይንተ ሕዝቦች አዘጋጀ። አንደኛው የምርጫ ድምጽ መስጠቱ ሊጀመር ጥቂት ቀናት ሲቀሩት በመስቀል አደባባይ የተጠራው ሰልፍ ነበር። በዚህ ሰልፍ ኢሕአዴግ የመንግሥት ጡንቻውን በማሳየት ከምርጫ ሥነ-ምግባር ሕግ ውጭ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶችንና ለመንግሥት ሥራ የተመደቡ መኪኖችን ደጋፊዎቹን ለማጓጓዝ ተጠቅሟል።

ኢሕአዴግ የመንግሥት መዋቅሩን በመጠቀምና ተጽዕኖ በማሳደር በርካታ ሕዝብ በመስቀል አደባባይ ላይ ቢያሰባስብም ሕዝቡ ያስተጋባው *«ዛሬ ለካናቴራ ነገ ለባንዲራ»* የሚለውን መፈክር ነበር። ሆኖም በተሰበሰበው ሕዝብ ብዛት እጅግ የረካው መለስ ንግግር ሲያደርግ ሰልፉን በማዕበል መስሎት ማዕበሉን ማቸነፍ እንደማይቻል በልበ ሙሉነት ገልጾ ነበር። ኢሕአዴግ የመስቀል አደባባዩን ሰልፍ አስከትሎ በየቀበሌውና በየክፍለ ከተማው ሕዝቡ ኢሕአዴግን በመደገፍ ሻማ እንዲያበራና ሻማ ይዞ በየአደባበዩ እንዲንቀሳቀስም ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር። ሆኖም ሻማዎቹን ይዘው ሲንቀሳቀሱ የነበሩት ሳይቀሩ ለምን በምሽት ቤታችንን ዘግተን ልጆቻችንን ጥለን እንንከራተታለን ብለው ያማርሩ ነበርና ሻማዎቹ ለኢሕአዴግ ብርሃን አልፈነጠቁለትም።

የምርጫ ቅስቀሳው ዘመቻ ሊጠቃለል ጥቂት ቀናት ሲቀረው ተቃዋሚዎች በአዲስ አበባ የድጋፍ ሰልፍ ሲጠሩ መስቀል አደባባይ ላይ ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ በአጠቃላይ

ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እልፍ አእላፍ ተሰለፉ። ወጣቱ፣ ሴቱ፣ አዛውንቱ፣ ድኻው፣ ባለሀብቱ፣ ምሁሩ፣ ወዘተ… በነቂስ ሰልፍ ወጣ። በተለይ ወጣቶች የተለያዩ መፈክሮችን አንግበው በከፍተኛ ወኔ ተንቀሳቀሱ። *«ንቦ ደሀና ሁኚ፤ ንቦ አትናደፊ፤»* እያሉ እየዘመሩ መስቀል አደባባይ እግር የሚያርፍበት ቦታ ጠፋ። ይህ ሁሉ ሕዝብ የተንቀሳቀሰው በራሱ ተነሳሽነት እንጂ እንደ ኢሕአዴግ ሰልፍ ተከፍሎት አልነበረም። ይህ ክስተት ኢሕአዴግ ቢያንስ በአዲስ አበባና በከተሞች አካባቢ እንደሚሸነፍ በማያወላዳ ሁኔታ ያረጋገጥ ነበር።

## *5.3 በምርጫ ሂደቱ አላስፈላጊ ቅስቀሳዎች*

### *5.3.1 የገዢው ፓርቲ ኢንተርሃምዌ መጣብህ ቅስቀሳ*

ምንም እንኳን በፖሊሲ ጥያቄዎች ዙሪያ ቅስቀሳዎች ቢኪያሂዱም በምርጫ 97 የምረጡኝ እንቅስቃሴዎች በርካታ አላስፈላጊና የሕዝብን ሥነ-ልቦና የሚነኩ ቅስቀሳዎች ተደርገዋል። በዚህ ረገድ አላስፈላጊውን ዘመቻ የጀመረው ኢሕአዴግ ቢሆንም ተቃዋሚዎችም ከኢሕአዴግ ያላነሰ አስተዋፅኦ ነበራቸው ለማለት ይቻላል። ኢሕአዴግ ከባሕርይው የተነሣና ሳይገምተው ሥልጣኔን ልነጠቅ ነው ብሎ የደረሰበት ሥጋትና ፍራቻ ለማርገብ በሕዝቡ ሥነ-ልቦና ላይ መጥፎ ጠባሳ የተወ የቅስቀሳ ስልቶችን ተጠቅሟል። ኢሕአዴግ በምርጫው አጉልቶ ያወጣው የፖሊሲ አቅጣጫ የብሔር ብሔረሰቦች መብቶች መጠበቅ አለባቸው የሚለውን ነበር። ኢሕአዴግ አቅጣጫውን በአግባቡ ከማራመድ ይልቅ ተቃዋሚዎች የብሔር ብሔረሰቦችን መብቶች ለመርገጥና ለማፈን እንደቆሙ አስመስሎ ለማቅረብ ብርቱ ጥረት አድርጓል። ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎችን በዚህ በመወንጀሉ አልበቃ ብሎት በአደባባይ ሲጠቅሰው የነበረውን የምርጫ ሥነ-ምግባር መመሪያ ጥሶ *«ኢንተርሃምዌ መጣብህ»* የሚለውን ፕሮፓጋንዳውን በተቃዋሚዎች ላይ ያራግብ ነበር። ኢንተርሃምዌ እ.አ.አ. በ1994 ዓ.ም. ሩዋንዳ ውስጥ ቱትሲዎችን ያለ ምሕረት በመጨፍጨፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙ የሁቱ ሚሊሻዎች ድርጅት ነው። ኢንተርሃምዌ ከስምንት መቶ ሺሕ በላይ ቱትሲዎችንና ለዘብተኛ ሁቱዎችን የጨፈጨፈ ድርጅት ነው። ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎችን ከኢንተርሃምዌ ጋራ ሲያመሳስላቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝብንና ብሔርን ላጥፋ ብሎ የተነሣ ፓርቲ እንዳልነበር ጠፍቶት ሳይሆን በቅስቀሳው፤ 1ኛ/ ሕዝቡን በተለይ ደግሞ ጭቁኖች የሚላቸውን ብሔር ብሔረሰቦች በማስደንገጥ ድጋፋቸውን ለመግዛት፣ 2ኛ/ በከፍተኛ ደረጃ እየተገዳደሩት የነበሩትን የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘር ማጥፋት ክሶ እርምጃ ሊወስድባቸው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነበር።

በደፋ ይሰሙ ከነበሩት ቅስቀሳዎች በተጨማሪ ውስጥ ውስጡን መሠሪ ወሬዎችም ይነዙ ነበር። በተለይ ተቃዋሚዎች ሥልጣን ከተቆጣጠሩ ደርግ በትግራይ ሕዝብ ያደርስ የነበረው ግፍ ይደገማል፤ ወደር የለሹ የሐውዜኑን ጭፍጨፋ የሚመስሉ ሌሎች ጭፍጨፋዎች በተቃዋሚዎች ይፈጸማሉ እያሉ ይቀሰቅሱ ነበር። ከዚህ ሌላም ምንጫቸው ያልታወቁና እስከ ዛሬ ድረስ ማን እንደጻፋቸው ምንም ማረጋገጫ ያልተገኘላቸውን በራሪ ጽሑፎችን እያጣቀሱ ተቃዋሚዎች፤ *«ትግሬ ወደ መቀሌ ዕቃው ወደ ቀበሌ»* ብለዋል በማለት በትግራይ ሕዝብ ሥነ-ልቦና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በማሳደር ድጋፍ እንዲሰጣቸው ተንቀሳቅሰዋል። እነዚህ ጽሑፎች በተቃዋሚዎች የተጻፉ ይሁኑ በኢሕአዴግ ወይም ኢሕአዴግ በተቃዋሚ ድርጅቶች ባሠረጋቸው ግለሰቦች እስከዛሬ የሚታወቅ ነገር የለም። ከዚህ ሌላ ኦሮሞዎችንና የደቡብ ብሔርና ብሔረሰቦችንም ትምክሕተኛው አማራ ሊውጣችኹ ነው እያሉ ቅስቀሳቸውን አጧጥፈው ነበር።

ኢሕአዴግ ይኸን መሰል ሕዝብን ከሕዝብ የሚያራርቅና የሚያቃቅር ቅስቀሳ የመረጠው በሥርዓቱና በሚያራምዳቸው ፖሊሲዎች ዙሪያ ያጋጠመውን ጊዜያዊ ሽንፈት ለመሸፈን ብቻ ሳይሆን ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የሚከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ አቅጣጫ ራሱ በጠላትነት ላይ የተመሠረተ ስለነበርም ነው። ኢሕአዴግ ዛሬም ቢሆን ኅብረተሰቡን እንደ ጠላትና እንደወዳጅ ከፋፍሎ እያናቆረ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚከጅል ፓርቲ ነው። ጨቋኝና ተጨቋኝ መደቦች ብቻ ሳይሆኑ ጭቁን የሚላቸውን ብሔር ብሔረሰቦችም በወዳጅነት፣ ጨቋኝና ትምክሕተኛ የሚለውን የአማራውን ክፍል ደግሞ በጠላትነት ይከፋፍለዋል። የኢሕአዴግ በጠላትነት የመፈረጅ አባዜ ጨቋኝና ትምክሕተኛ በሚለው የአማራ ገዥ መደብ ብቻ ሳያበቃ በኦሮሞውና በሌሎች ብሔሮች ኢሕአዴግን የሚቃወሙ *«ጠባብ»* ድርጅቶችንና ግለሰቦችንም ይጨምራል። በምርጫው ጊዜም ይህን አፈራረጁን በመለጠጥ ትግሬውን፣ ኦሮሞውንና ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችን አማራው መጣባችሁ፤ አማራውን ደግሞ የኦሮሞ ብሔርተኞች ሊያጠፏችኹ ነው እያለ የተጨነቀ ሥነ-ልቡና በመፍጠር ድጋፍ ሊያሰባስብ ሞክሯል።

ኢሕአዴግ ወዳጅና ጠለት፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ፣ ጠባብና ትምክሕተኛ፣ በሚል ኅብረተሰቡን የሚከፋፍለውን የፖለቲካ አቅጣጫ ቢከተልም በራሱ ትንታኔ እንኳን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጨቋኝ ተብሎ የሚፈረጀው ማን እንደሆነ ግልጽ አላደረገውም ነበር። ለአስራ አራት ዓመታት ያኸል የፖለቲካ መዋቅሮችን ያልተቆጣጠረ፣ የአገሪቱን የፖሊሲ አቅጣጫዎች የማይነድፍና የማይተገብር፣ ሕግ የማውጣት ሥልጣን የሌለውና የአገሪቱን ሀብት የማያስማራ መደብ እንዴት ጨቋኝ ሊሆን ይችላል? እንዴትስ ሥልጣን ከተቆጣጠረው ከኢሕአዴግ በላይ አደገኛ ሊሆን ይችላል? በኢሕአዴግ አገላለጽ ትምክሕትን የሚወክለው ኃይል ደርግ ነበርና ደርግ ከሥልጣን ተወግዶ ከተንኮታኮተ ከዓመታት በኋላ የኢሠፓም ይሁን የደርግ አቀንቃኞች አንሰራርተው ለኢትዮጵያ ሥጋት ይፈጥራሉ ማለቱ የራሱን ችግር ለመደበቅና ሕዝቡ ያለፈው እንዳይመለስብኝ ብሎ እየባነነ ለዘለዓለም እንዲመርጠው ለማድረግ የቀየሰው ዘዴ ነበር።

## *5.3.2 የተቃዋሚዎች ፓርቲንና ሕዝብን ያልለየ ቅስቀሳ*

ተቃዋሚዎችም ቢሆኑ የፖሊሲ ጥያቄዎችን አንሥተው ቢቀሰቅሱም ኢሕአዴግ ሲጠቀምበት የነበረውን የኢንተርሃምዌ መጣብህ ዓይነት የቅስቀሳ ስልት አልተጠቀሙም አይባልም። በተለይ ህወሓት/ኢሕዴግንና የትግራይን ሕዝብ እንደ አንድ በመውሰድ ለህወሓት/ኢሕአዴግ የነበራቸውን ጥላቻና ተቃውሞ ሕዝቡን ባካተተ መልኩ ያንጸባርቁት ነበር። የትግራይንም ሕዝብ በተለየ መልኩ ተጠቃሚ እንደሆነ እያስመሰሉ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋራ እያጋጩት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሞከሩ ተቃዋሚዎች አልጠፉም። የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ በተለየ ተጠቀሚ ሆኗል የሚለው አስተሳሰብ ገና ህወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን ሲቆጣጠር የተከሰተ ሲሆን አንዳንድ መሠረታዊ የዘረኝነት ችግር የነበራቸው ግለሰቦች የሚያራምዱት ነበር። እነዚህ ግለሰቦች የመኻል አገር ሀብት */በምዩዚየም የነበረው ቅርሳ ቅርስ ሳይቀር/* ወደ ትግራይ እየተጋዘ ነው፤ የትግራይ ተወላጆች አገሪቱን ሊመሩ አይገባም፤ የትግራይ መሪዎች ወገኖቻቸውን እየጠቀሙ ነው የሚል ፕሮፓጋንዳ ይነዙ ነበር። በምርጫ 97 የተሳተፉ አንዳንድ ፓርቲዎችም ከዚህ አመለካከት ባይጸዱም በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የነበረው ችግር፣ ሰቆቃ፣ ድኽነት፣ ሙስናና ብልሹ አስተዳደር በትግራይም ተንሰራፍቶ እንደነበር ለመገንዘብ ዓቅም አልነበራቸውም ብዬ አልገምትም። ቢያንስ አንድ የፖለቲካ ሥርዓት ከመሠረቱ ከተበላሸ ለአንድ አካባቢ ሕዝብ ሰይጣን፣ ለሌላው አካባቢ ሕዝብ ደግሞ መልአክ፣ ሊሆን እንደማይችል በንድፈ ሐሳብ ደረጃ እንኳን ሊገነዘቡ ይችሉ ነበር። እንዲያውም አገዛዙ

ጓሮዬ በሚለው አካባቢ ስንጥቅ እንዳይፈጠር የጭቆና ቀንበሩን ይበልጥ እንደሚጭን መገንዘብ ነበረባቸው።

ከመሠረታዊ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት እድገትና ልማት አንጻር ትግራይ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል በተለየ የመጠቀበት ሁኔታ አልነበረም። በእርግጥ አሉባልታን አስተካክሉ ለዚሁ የሚመቹ አኃዞችን አቀነባብሮ እውነትም ሆነ አልሆነ የትግራይ ሕዝብ በተለየ ሁኔታ ተጠቀሚ ሆኗል የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚዳዳው ክፍል ይህን ማለቱ አይቀርም። በተጨባጭ ሲታይ ግን ከህወሓት/ኢሕአዴግ በስተቀር ሌላ ፓርቲ እንዳይቀበል በጥብቅ የተከለከለውና ከህወሓት ውጭ ሌላ ፓርቲ ቢከተል ፍዳው የሚበዛበትና ይበልጥ ተጽዕኖ የሚደረግበት የትግራይ ሕዝብ ነበር። ህወሓት የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን ዘንግቶ በትግራይ እንደሚወደሱት በርካታ ቅዱሳን እንዲወደስ ይበልጥ ጫና ያደርግ የነበረው በትግራይ ሕዝብ ላይ ነበር። ከሰብአዊ መብቶች ጥበቃ አንጻርም የትግራይ ሕዝብ በእጅጉ የተሰቃየና በየጊዜው በሚኪያሄዱበት ግምገማዎች፣ ሲያስፈልግም እስርና ወከባ፣ ተሸማቅቆ የሚኖር ሕዝብ ነበር። ግለሰባዊ ነጻነቱ ተነፍጎ ልክ እንደ ሠራዊት በጠበቀ ማዕከልነት /ጥርናፈ/ ተሸብቦ እንዲኖር የተበየነበት ሕዝብ ነበር። በትግራይ የነበረው ሥራ አጥነት ከሌላው ክልል የከፋ እንደሆነ እንጂ የተሻለ አልነበረም። ብዙ ወጣቶች ከአካባቢው እየፈለሱ በመኻል አገርና በየዓረብ አገሩ ይንከራተቱ የነበረው ከዚህ አስከፊ ሥራ አጥነት የተነሣ ነበር። ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኅብረተሰብ ክፍልም በዕለት ደራሽ እርዳታና በሴፍቲኔት የታቀፈ ነበር። ለነገሩ ይኸን ኹሉ ከምርጫ 97 ጋራ አያይዤ እንዳለፈ ታሪክ አወሳኹት እንጂ ዛሬም ቢሆን የትግራይ ሕዝብ አላለፈለትም። ስለዚህ እነዚህን ሁሉ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች የተሸከመውን የትግራይ ሕዝብ የሥርዓቱ ልዩ ተጠቃሚ ነው ብሎ መቀስቀስ ከጤነኛ የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚመነጭ አልነበረም።

የወቅቱ ተቃዋሚዎች የትግራይን ሕዝብና ህወሓትን ያለመለየት ችግር የሚጀምረው ከህወሓት ስያሜያቸው ነበር። ምንም እንኳን ህወሓት «ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ» ተብሎ ቢጠራም ተቃዋሚዎች ህወሓትን የሚጠሩት ወያኔ ብለው ነበር። ወያኔና ህወሓት አንድ አይደሉም። ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ሥነ-ልቡና ከፍተኛ ቦታ ያለው የአልገዛምና የእምቢተኝነት መገለጫ ነው። ህወሓትም ይህን ስያሜ የመረጠው የሕዝቡን የቆየ ሥነ-ልቡና ለማጋራት ነው። ይኽ ሆኖ ሳለ የዛሬውን የትግራይን ሕዝብ ሳይቀር አንቀጥቅጦ የሚገዛውን አምባገነኑን ህወሓት ወያኔ ብሎ መጥራት የሕዝቡን እምቢ ለጭቆና፣ እምቢ ለአድልዎ፣ መንፈስ የሚደመስስ ነው። ይህን የወያኔ ሕዝባዊ መንፈስ ያልተገነዘበ የአንዳንድ ተቃዋሚዎች አነጋገር ህወሓትንና የትግራይን ሕዝብ አንድ አድርጎ ማየቱ መቃቃርና መራራቅን ለመፍጠር ካልሆነ በስተቀር ሌላ ፋይዳ አልነበረውም።

ሌላው ምናልባት የትግራይ ሕዝብ በተለየ ተጠቅሟል ለማለት አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች ሲያራግቡትና ጊዜያዊ ትርፍ ለማግኘት ሲቀሰቅሱበት የነበረው ጉዳይ የትእምት /ኤፈርት/ ኩባንያዎች የትግራይን ሕዝብ ጠቅመዋል የሚለው ነበር። ሆኖም የትግራይ ሕዝብ ከነዚህ የንግድ ኩባንያዎች ያተረፈው መሠረታዊ ጥቅም አልነበረም፤ ምክንያቱም ኩባንያዎቹ በህወሓት አመራር ቁጥጥር ሥር ሆነው ለከፍተኛ ምዝበራና ለዘመድ አዝማድ መጠቀሚያ ተዳርገው ነበርና። ምናልባት የተወሰነ ሥራ በመፍጠር ረገድ አካባቢውን ጠቅመዋል ሊባል ይችል ይሆናል። ሆኖም እነዚህ ኩባንያዎች ባይኖሩም ኖሮ የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት ማለትም እብነ በረዱን፣ የሲሚንቶ ድንጋዩን፣ ቆዳውን፣ ሰሊጡን፣ ወርቁን፣ ሌላውን ማዕድንና የአካባቢውን የሰው ኃይል ለመጠቀም የሚሹ ኩባንያዎች በአካባቢው መተከላቸው አይቀርም ነበር። ታድያ ትእምት ባይኖርስ ይህን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠቀም የሚፈልጉ ኩባንያዎች መተከል የትግራይን ሕዝብ ልዩ ተጠቃሚ ያደርገዋል ማለት ነው? ለማንኛውም

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ትእምት በትግራይ ሕዝብ ስም የሚነግድ የጥቂቶች ሀብት እንጂ የትግራይ ሕዝብ የሚያዝበትና ባለድርሻ የሆነበት ተቋም እንዳልሆነ ተቃዋሚዎቹ መገንዘብ ነበረባቸው።

ተቃዋሚዎች ለፖለቲካ ትርፍ ሲሉ ገዢውን ፓርቲና ሕዝቡን፣ ምርትና ግርዱን፣ አለመለየታቸው በተለይ መኻል አገር ይኖሩ በነበሩ በርካታ የትግራይ ተወላጆች ዘንድ ሥጋትን ፈጥሮ ነበር። ይህ በምርጫው ሂደት ዐልፎ ዐልፎ ሲከሰት የነበረውን የትግራይ ሕዝብና ህወሓትን እንደ አንድ የማየት አባዜ በምርጫው ማጠቃለያ ላይ በአንድ የቅንጅት ሰው በአደባባይ «ኢሕአዴጎች ወደ መጡበት ይመለሳሉ» ተብሎ ተገልጿል። እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ኢሕአዴግ ጨቋኝ ፓርቲ ቢሆንም ትግራይን ብቻ የሚወክል እንዳልሆነና ከኢትዮጵያ የተፈጠረ እንደሆነ ነው። ተቃዋሚዎችም ይኸን ተረድተው የሚቃወሙት የኢሕአዴግን ሥርዓትና ፖሊሲ እንጂ ኢሕአዴግ እወክለዋለሁ የሚለውን ሕዝብ መሆን አልነበረበትም። እንዲኽ ዓይነት አኪያሄድ የነበራቸው ተቃዋሚዎች ከኢሕአዴግ ይሻሉ ነበር ለማለት ያስቸግራል።

በአጠቃላይ በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ቅስቀሳ አንዳንድ ተቃዋሚ ድርጅቶች አቅጣጫን የሳተ፣ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጭና በሕዝቡ ዘንድ ጥርጣሬን የሚያሳድር የቅስቀሳ ስልት ተከትለዋል። አልገባቸውም እንጂ በዚህ አኪያሄዳቸው የጠቀሙት ለዘልዓለም በሥልጣን ለመቆየት የሚከጅለውን ኢሕአዴግን ብቻ ነበር። ኢሕአዴግ ራሱ በፈጠረውና አንዳንድ ተቃዋሚዎችም ባስተጋቡት የፍርሀት ድባብ ምክንያት ብዙ የትግራይ ተወላጆች በገዛ አገራቸው በሥጋት እንዲኖሩና አማራጭ አጥተው የኢሕአዴግን ከለላ እንዲሹ አድርጓቸዋል። የተቃዋሚዎች ዓላማ እኛን ማጥፋት ከሆነ ያው የምናውቀው ሰይጣን ይሻለናል ያሉ የትግራይ ተወላጆችም ቁጥራቸው ጥቂት አልነበረም። ለህወሓት/ኢሕአዴግ አንዱ የሥልጣን መሠረት የሆነውም የእነዚህ በሥጋት የተዋጡ ዜጎች ሥነ-ልቦና ነው።

## *5.4 የተቃዋሚዎች ኅብረትና ኢሕአዴግ ያልጠበቀው የምርጫ ውጤት*

### *5.4.1 የተቃዋሚዎች ኅብረት*

በምርጫ 97 ከፍተኛ ተጽዕኖ ካሳደሩት ተግባራት አንዱ ሁለት ትላልቅ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ኅብረት መፈጠራቸው ነበር። አንዱ ኅብረት *«ቅንጅት»* በሚል ይጠራ የነበረው ሲሆን የአራት ፓርቲዎች ማለትም የቀስተ ደመና፣ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲና /ኢዴፓ/ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሊግ /ኢዴሊ/ ስብስብ ነበር። የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት በወቅቱ ቀስተ ደመና ከፍተኛ ምሁራንን፣ ኢዴፓ ወጣቱን፣ መኢአድ ነባር ፖለቲከኞችን ያሰባሰበ የነበሩ ሲሆን የኢዴሊ ፖለቲካዊ መሠረት እምብዛም አይታወቅም ነበር። የቅንጅት መሠረትም ሊበራል የፖለቲካ አስተሳሰብ ሆኖ ለግል ነጻነቶችና መብቶች ትኩረት ይሰጥ ነበር።

ሁለተኛ ስብስብ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ኃይሎች በሚል ይታወቅ የነበረው ሲሆን በዚህ ስብስብ እንደነ ደቡብ ኅብረት፣ የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ /ኢሶዴፓ/፣ የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ /ኦብኮ/፣ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦፌዴን/፣ ያሉ ብሔራዊና ኅብረ ብሔራዊ ድርጅቶች ተካተው ነበር። ከኢትዮጵያ ውጭ የሚንቀሳቀሱት ነባር የፖለቲካ ፓርቲዎችም ማለትም ኢሕአፓ፣ መኢሶንና ኢዴኅ በዚሁ ስብስብ ተካተው ነበር። ይህ ስብስብ በአብዛኛው የብሔር ብሔረሰቦች መብት በቂ ቦታ

እንዲያገኝ የሚታገሉ ድርጅቶችን ያቀፈ ሲሆን የድርጅቶቹ የፖለቲካ ራዕይ ከቀኝ ሊበራል ዴሞክራሲ እስከ ግራ ሶሻል ዴሞክራሲ ያለውን የፖለቲካ አመለካከት የሚሸፍን ነበር።

በምርጫ 97 የታየው ታላቅ እምርታ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በሰማንያና በዘጠና ፓርቲዎች ከመከፋፈል ኢሕአዴግን ጨምሮ በሦስት ታላላቅ ስብስቦች መጠቃለሉ ነበር። እንዲያውም ሁለቱ ተቃዋሚ ስብስቦች ማለትም ቅንጅትና ኢዴኢኃ ወደ አንድ ስብስብ ለመጠቃለል ሙከራ ያደረጉበት ጊዜም ነበር። ይህ የተቃዋሚዎች ተቀናጅቶ የመሥራት አዝማሚያ ባይሰምርም ሁለት ትላልቅ የተቃዋሚ ጎራዎች መፈጠራቸውም ራሱ ለሕዝቡ ትልቅ ፋይዳ ነበረው።

በምርጫ 97 ወቅት መፍትሔ ያላገኘው አንዱ ትልቁ ጉዳይ ግን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሰባስቦ መደራጀት በስብስቡ የሚያስከትለው ተጽዕኖ አስቀድሞ ያለመታወቁ ነበር። ኢሕአዴግ በደነገገው ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ ሁለት ዓይነት አደረጃጀት ማለትም ኅብረ ብሔራዊና ብሔራዊ ወይም ክልላዊ አደረጃጀት ነበሩ። የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ከመቀረጹና የምርጫ ሕጉ ከመጽደቁ ቀደም ብሎ በስድሳዎቹ ገደማ የተፈጠሩት ከላይ የጠቀስኳቸው ድርጅቶች አንዳንዶቹ ኅብረ ብሔራዊ ሌሎች ደግሞ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ነበሩ። በኅብረ ብሔራዊነት ከተደራጁት ቀደምት ድርጅቶች መኻል ኢሕአፓንና መኢሶንን መጥቀስ ይቻላል። በብሔራዊ ወይም ክልላዊ መልክ ከተደራጁት ድርጅቶች መኻል ደግሞ አነግ፣ ህወሓት፣ ምሶነግ፣ አነግና ሲአን ሊጠቀሱ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ ሁለቱን አደረጃጀቶች ቢቀበልም ከነዚህ አደረጃጀቶች በስተጀርባ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ነበር። ኅብረ ብሔራዊ ድርጅቶች የመደራጀት መሠረታቸው መደብ ወይም የግለሰብ ነጻነት ላይ ያተኮረ ሲሆን የብሔራዊ ወይም የክልላዊ ድርጅቶች ዋነኛ ትኩረት ደግሞ የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ማስጠበቅ ላይ ነበር። እነዚህ ሁለት አደረጃጀቶች አብረው የሚሠሩበትና የሚደራጁበት ሁኔታ ያልተለመደ እንደመሆኑ በምርጫ 97 ይኸው ችግር ተከስቶ ነበር። ቅንጅት በብሔር የተደራጀ ፓርቲ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ከሚል አስተሳሰብ ተነሥቶ ይመስላል በፈጠረው ስብስብ ብሔር ወይም ክልል ተኮር ድርጅቶች እንደማይካተቱ ይፋ አድርጎ ነበር። በመሆኑም ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ዐሸን የፈሉት ብሔር ተኮር ድርጅቶች ቅንጅትን በከፍተኛ ጥርጣሬ ይመለከቱት ነበር። ቅንጅቶች ይህን አቋም ማራመዳቸው መብታቸው ቢሆንም ኢትዮጵያ የተጓዘችበትን መንገድና ያለችበትን የእድገት ደረጃ ያገናዘበ ነበር ለማለት ግን ያስቸግራል። በስትራቴጂ ደረጃ በኢትዮጵያ ጠንካራ አገር ዐቀፍ ፓርቲዎችን ፈጥሮ ለአገራዊ አጀንዳዎች ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራቱ ተገቢ ቢሆንም ይህን እውን ለማድረግ ግን በብሔር ወይም በክልል የተደራጁ ፓርቲዎችን አላቅፍም ማለት ከስልትና ከመርሕ አንጻር ችግር መፍጠሩ አልቀረም።

አማራጭ ኃይሎች ኅብረ ብሔራዊና ብሔራዊ ወይም ክልል ተኮር ድርጅቶችን አሰባስበው ለመንቀሳቀስ ቢሞክሩም ጠንካራ አገራዊ ፓርቲ በመፍጠር ረገድ ስትራቴጂያዊ ግባቸው ምን ሊሆን እንደሚችል በግልጽ አላስቀመጡም ነበር። የዚህ ስብስብ ውጤት ግልጽ ሊሆን ይችል የነበረው ድርጅቶቹ በምርጫው ቀንቷቸው አብላጫውን የፓርላማ ወንበር ተቆጣጥረው ኢሕአዴግን የሚተካ መንግሥት ለማቋቋም ቢንቀሳቀሱ ነበር። ዳሩ ይኸ አልተሳካላቸውምና ከአደረጃጀታቸው ሊመነጭ ይችል የነበረውን የመንግሥት አወቃቀርና የሥልጣን ክፍፍል ውጤትምተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል።

በምርጫ 97 የተከሰተው ሌላው ችግር ድርጅቶቹ ተሰባስበው ለመሥራት ሲስማሙ በሰከነ መንገድ አስበውበት፣ የሚያስማሟቸውንና የሚለያዩዋቸውን ጉዳዮች በሚገባ አጢነው፣

የተራ አባሎቻቸውን ድጋፍ አግኝተው አለመሆኑ ነበር። ከዚህ የተነሣም እጅግ አጭር የሆነውን ምርጫውን የማቸነፍ ግብ ለማሳካት እንጂ ለዘላቂ ጉዞ የቀየሱት አኪያሄድ የነበረ አይመስልም። አንዳንድ የስብስቦቹ አባላት ሲያወሩ በአንድ ፖለቲካዊ ማዕቀፍ የተሰባሰቡ ሳይሆኑ አንዱ ሌላውን በጥርጣሬ የሚያይበትና ስም የሚያጠፋበት፣ እንዲሁም በአመራሩም እምነት የሌለበት ይመስል ነበር። በእርግጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተሰባሰቡ ድርጅቶች በመሆናቸው እንደዚህ ዓይነት ችግሮች መከሰታቸው አይቀርም ነበር። ሆኖም ያን ያህል ልዩነትና አለመተማመን ይዞ መጓዙ ደግሞ ለአብሮነታቸው አደገኛ ነበር። መጨረሻ ላይ የተከሰተው መጠላለፍና አለመግባባትም የዚሁ በችኮላ የመሰባሰብ ውጤት ነበር። በዚህ ዙሪያ እያልኩ ያለሁት መሰባሰቡ መልካም ሆኖ ድርጅቶቹ በተቻላቸው መጠን ለትብብራቸው መሠረት የሆኑትን የጋራ አቋሞችና አሠራሮች ማመቻቸት ነበረባቸው ነው።

## *5.4.2 ኢሕአዴግ ያልጠበቀው የምርጫ ውጤት*

ኢሕአዴግ ምርጫው ከመኪያሂዱ በፊት ተቃዋሚዎች ይገዳደሩኛል የሚል ግምት ጭራሽ አልነበረውም። ምርጫው ከመጀመሩ ከጥቂት ወራት በፊት አንድ የዱሮ ጓደኛዬ አንዱን የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሸራተን ሆቴል አግኝቶት *«የምርጫው ውጤት ምን ሊሆን ይችላል?»* ብሎ ሲጠይቀው ምርጫው ለኢሕአዴግ ብዙም አሥጊ እንዳልሆነና ተቃዋሚዎች ገፋ ቢል አስር በመቶ መቀመጫ ሊያገኙ እንደሚችሉ ነግሮት ነበር። የማዕከላዊ ኮሚቴው አባል ግምት የብቻው ሳይሆን የድርጅቱ መሪዎችን የጋራ ግምገማ የሚያንጸባርቅ እንደነበር መገመቱ አያስቸግርም። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው አስገራሚውን መስቀል አደባባይን ያጥለቀለቀውንና ተቃዋሚዎችን በማያወላዳ መንገድ ይደግፍ የነበረውን የሕዝብ ሰልፍ እሲኪያዩ ድረስ የኢሕአዴጎቹ ግምት ተቃዋሚዎች የትም አይደርሱም የሚል መሆኑ ነው። ከመስቀል አደባባዩ ሰልፍ በኋላም ቢሆን ይህ የተቃዋሚዎች ድጋፍ እጅግ አነስተኛ ውክልና በነበራቸው በከተሞች ብቻ እንደተወሰነ እንጂ ገጠሩ የኢሕአዴግ ደጋፊ እንደሆነ ያምኑ ነበር። ኢሕአዴጎች ከፍተኛ የተወካይ ቁጥር የነበረው አዲስ አበባ ለአገሪቱ በአጠቃላይ ከሚደርሰው ዐምስት መቶ አርባ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫዎች ኻያ ሦስት ብቻ ይደርሰው ስለነበር ሌሎች ታላላቅ ከተሞችም ከአንድ መቀመጫ በላይ ስለማይወክሉ ተቃዋሚዎች ሁሉን ታላላቅ ከተሞች ቢያሸንፉ እንኳን የሚያገኙት ድምጽ ከአርባ አይበልጥም የሚል ስሌት ነበራቸው።

ከላይ እንደገለጽኩት፣ ኢሕአዴግ በተለያየ መንገድ ራሱን እያጽናና እጅግ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ድምጽ ተሰጥቶ ከተቆጠረ በኋላ፣ ተቃዋሚዎች በበርካታ አካባቢዎች ማቸነፋቸውና የአዲስ አበባን የሕዝብ ተወካዮችና የከተማ ምክር ቤት መቀመጫዎች ጠራርገው እንደወሰዱ ታወቀ። በሌሎች ከተሞችና በገጠር አካባቢዎችም ከፍተኛ የማቸነፍ ዕድል እንዳላቸው ተሰማ። በዚህ ጊዜ በኢሕአዴግ ጎራ ከፍተኛ ድንጋጤ ተፈጠረ። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም ወድያውኑ ጊዜያዊ አዋጅ መሰል በአዲስ አበባ ከተማ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጎ የምርጫ ድምጹ ተቆጥሮ ሳያልቅ ኢሕአዴግ አሸናፊ መሆኑን አስታወቀ። በየቀኑ የሚገለጹት የምርጫ ውጤቶች ግን ትላልቆቹ የኢሕአዴግ መሪዎች እንደተዘረሩ ይፋ የሚያደርጉ ነበሩ። ከአዲስ አበባ ውጪ በረኸት ስምኦን፣ አባዱላ ገመዳ፣ ወርቅነህ ገበየሁ፣ ወዘተ… ሲሸነፉ እነ አዲሱ የተመረጡበት አግባብም ብዙ ውዝግብ ያስነሣ ነበር። በወቅቱ ኢሕአዴግ ተቃዋሚ ተወዳዳሪዎች ባልተሰማሩበት በትግራይና በተወሰኑ የገጠር አካባቢዎች ካልሆነ በስተቀር በፍጹም በዝረራ ቢሸነፍም ሥልጣኑን ለማስረከብ ግን ጭራሽ ዝግጁ አልነበረም።

በአንድ በኩል ኢሕአዴግ ምርጫውን አሸንፌያለሁ ብሎ ሲያውጅ በሌላ በኩል ተቃዋሚዎች ምርጫውን ያሸነፍነው እኛ ነን ሲሉ ከፍተኛ ውዝግብ ተፈጥሮ በመጨረሻ ይህ ወደ ሰልፍና ተቃውሞ አመራ። በዚህ ጊዜ ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎችንና ሰልፈኞችን በአስለቃሽ ጢስና በቆመጥ ሳይሆን በጥይት ደበደበ፤ በየአካባቢውም የእዝ ማዕከሎችን አቋቁሞ የጦር ኃይል አባላትን አሰማራ፤ የውጭ ጠላት እንዲመክት የተዘጋጀውን ኮማንዶ ጦርንም ተጠቀም። በሠለጠኑ አገሮች /ለነገሩ ሥራ ላይ ባልዋለው በኛም ሕገ መንግሥት/ የጦር ኃይሉ ገለልተኝነት የሚረጋገጠው እንዲህ ባሉ የምርጫ ውዝግቦችና ምርጫን ተከትሎ የሚነሣን ዐመፅ ለማስታገስ በሚደረገው እንቅስቃሴ ነው። የዚህ ዓይነቱን ዐመፅ የመቆጣጠሩ ኃላፊነት የሚሰጠውም ለፖሊስ ነው። ሆኖም ኢሕአዴግ በፍርሀት ተውጦ ስለነበር በገዛ ዜጎቹ ላይ የኮማንዶ ጦር ብቻ ሳይሆን ታንኮችና መድፎችንም ለማሰማራት ተዘጋጅቶ ነበር።

ኢሕአዴግ ያመነው ብቻ ቢጠቀስ እንኳን በአዲስ አበባ መቶ ዘጠና ሦስት ዜጎች ሲገደሉ በርካታዎች ቆስለዋል። የተቀሰቀሰው ቀውስ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይወሰን ወደ ክልሎችም ለምሳሌ ወደ ወሎ፣ ጎንደር፣ ምዕራብ ጎጃም፣ አዋሳና አካባቢው፣ ወዘተ… ተዛምቶ ነበር። በነዚህም አካባቢዎች የዜጎች ሕይወት ጠፍቷል፤ ለአካል ጉዳት የተዳረጉትም ቁጥራቸው ቀላል አልነበረም። ከዚህ ሌላ ኢሕአዴግ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን አፍሶ ለእስር ዳርጓል። በዚህ የእስር ዘመቻ ከአዲስ አበባ ብቻ ከሠላሳ ሺሕ በላይ ወጣቶች ታፍሰው በደዴሳ፣ በሸዋ ሮቢት፣ በዝዋይ፣ በብር ሸለቆ፣ ታጉረው ነበር። በነዚህ የእስር አካባቢዎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ወጣቶች ያለ በቂ ምግብ፣ መጠለያና ሕክምና ታስረው ለወባ፣ ለሌሎች በሽታዎችና ለሞት ተጋልጠው ነበር። ከሠላሳ ዓመት በፊት ዜጎች በሰላማዊ መንገድ ተቃውሟቸውን የማሰማት መብታቸው መረጋገጥ አለበት የሚለውን መፈክር አንግበው ሲፋለሙ የነበሩት የኢሕአዴግ መሪዎች ከሥልጣናቸው ላለመፈናቀል በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን አስረውና ከመቶ ዘጠና በላይ ዜጎችን ገድለው ዐረፉት።

ኢሕአዴግ ይህን ሁሉ ሲያደርግ ይሰጠው የነበረው ምክንያት ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን የማስጠበቅ፣ የዜጎችን ደኅንነት የማረጋገጥና የአገሪቱን ሀብትና የዜጎችን ንብረት ከውድመት የማዳን ኃላፊነት እንዳለበት ነበር። ታድያ ይኸን ኃላፊነት ያልታጠቁ ዜጎችን በጦርነት አግባብ በጥይት በመግደል ብቻ የሚወጡት ነበርን? ይኸ እስካሁን መልስ ያላገኘለት ጥያቄ ቢሆንም በወቅቱ ለጥያቄው የተሰጠው መልስ እጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ ነበር። የቻይና ኮምዩኒስት ፓርቲ መሪዎች ቲዬን አን ሜን አደባባይ ላይ ሰልፍ የወጡትን ወጣቶች በታንክ ጭምር ከፈጁ በኋላ፤ «ይህን ያደረግነው ሰልፍ የመቆጣጠር ልምድ ስላልነበረን ነው» እንዳሉ ሁሉ ኢሕአዴግም፤ «በዜጎች ላይ ጥይት ለመተኮስ የተገደድነው አስለቃሽ ጢስ ተጠቅሞ ዐድማ የሚበትን ኃይል ስላላዘጋጀን ነው» ብሎ ተናገረ። በአጭር ጊዜ ውስጥ የኤርትራን ጦር ድባቅ የሚመታ ጦር ለማዘጋጀት የቻለው መንግሥት ዐድማ በታኝ ፖሊስና አስለቃሽ ጋዝ ለማዘጋጀት አልቻልኩም ሲል ራሱን የሚያስገምተው ነበር። ኢሕአዴግ ይህን ያደረገው ዐመፅ የሚቆመው ዐመፀኞችን በማያዳግም ሲቀጡ ነው የሚለውን የቀድሞ ሥርዓቶች አስተሳሰብ መሠረት አድርጎ እንደሆነ ግልጽ ነበር። ባይሆንማ በኻያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በመቶ ሚልዮኖች የሚገመት የጦር መሣሪያ የሚሸምት መንግሥት ሰላማዊ ዜጎችን ለመመከት ያለኝ ብቸኛ አማራጭ ጥይት ነው ባላለ ነበር።

ኢሕአዴግ ምርጫ 97ን እንዳላሸነፈ እያወቀና ምርጫው የተጭበረበረ መሆኑን ዓለም ዐቀፍ ታዛቢዎች ሳይቀሩ እየመሰከሩ ምርጫውን ያጭበረበሩት ተቃዋሚዎች ናቸው በማለት በተሸነፈባቸው አካባቢዎች ዳግም ምርጫ እንዲደረግ ጠየቀ። ከዚህ በኋላ የነበረው ጨዋታ

የነጻ፣ ፍትሐዊና ተአማኒነት ያለው ምርጫ መሆኑ ቀርቶ ጉልበትን ተጠቅሞ ሥልጣንን የማደላደል ሆነ። እንዲሁም የምርጫ ውጤቱን የያዘውን መኪና አድፍጠው ከዘረፉ በኋላ የተሸነፉበትን ምርጫ እንዲደገም አድርገው የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ተመራጭም፣ ታዛቢም፣ አስመራጭም፣ ድምጽ ቆጣሪም ሆነው በምርጫው እንዳሸነፉ አወጁ። ከመጀመሪያው ድምጽ ቆጠራ በኋላ በምርጫ ቦርድ እንደተቸነፉ የተነገራቸው እነ በረኸት ስምኦን፣ አባዱላ ገመዳና ሌሎቹም ባለሥልጣናትም ተመርጠናል ብለው በትረሥልጣናቸውን በጡንቻ ተቆጣጠሩ።

የምርጫው አኪያሄድ ትንተና እዚህ ያብቃና በምርጫ 97 ኢሕአዴግን ለሽንፈት ያበቁትን ምክንያቶች በመጠኑም ቢሆን መዳሰሱ ጠቃሚ ነው ብዬ እገምታለኹ። ኢሕአዴግ በምርጫ 97 የተሸነፈበት ዋነኛ ምክንያት ዴሞክራሲያዊ መስሎ ለመታየትና ተጨማሪ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የፖለቲካ ምኅዳሩን በመጠኑም ቢሆን ገርበብ በማድረጉ ነበር። ኢሕአዴግ የሕዝቡን ፍላጎት ሳይረዳ ጠንካራ ተቃዋሚ የለም በማለት ተማምኖ የፖለቲካ ምኅዳሩን ከፈት ማድረጉ ለሽንፈቱ ዋና ምክንያት ነበር። ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎች የትም አይደርሱም በሚል በሩን ገርበብ ማድረጉ ከዱሮው በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጁና እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ዕድል ሰጥቷቸዋል። በተፈጠረው ምቹ ሁኔታም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊዎቻቸውን አሰባስበው የጋራ ቅንጅት ፈጥረዋል። የተቃዋሚዎች በቅንጅትና በኅብረት መሥራት ለሕዝቡ ተስፋ ሰጥቶታል።

በምርጫ 97 ተቃዋሚዎች እንዲያሸንፉ የረዷቸው ሁለት ተጨማሪ ምክንያቶች ነበሩ። አንደኛው የውጭ ታዛቢዎች በብዛት መግባትና የምርጫ ሂደቱን ለመታዘብ መቻል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአገራችን ታሪክ በተነጻጻሪ የተሻለ የሚባል የሲቪል ማኅበረሰብ እንቅስቃሴ መታየቱ ነበር። የውጭ ታዛቢዎች በብዛት መገኘት በካድሬዎችና በኢሕአዴግ ተራ አባላት ብቻ ሳይሆን በኢሕአዴግ አመራር ላይም ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር። በወቅቱ ኢሕአዴግ ምርጫው ነጻና ፍትሐዊ አልነበረም እንዳይባል ለካድሬዎቹና ለአባላቱ ግልጽ በሆነ ሽፍጥ እንዳይሰማሩ መመሪያ ሰጥቷቸው ስለነበር ይህ በተወሰነ ደረጃ ልጓም አበጅቶላቸው ነበር። የሲቪል ማኅበረሰቡም ሕዝቡ መብቱን ተገንዝቦ የፈለገውን ፓርቲና ግለሰብ እንዲመርጥ ብርቱ እንቅስቃሴ አድርጎ ነበር። ከሁሉም በላይ ግን ሕዝቡ የውጭ ታዛቢዎች መኖራቸውን እንደ ዋስትና አይቶት ካለሥጋት የፈለገውን የፓርቲ ዕጩ ለመምረጥ ችሎ ነበር። በምርጫ 97 ተቃዋሚዎች የተከተሉት የቅስቀሳ ስልትም በምርጫው ላገኙት ድምጽ አስተዋፅኦ አድርጓል። በቴሌቪዥንና በሬድዮ የተሳተፉባቸው ክርክሮች በአመዛኙ በማይረቡ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን ወሳኝ በሆኑ አገራዊ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ላይ ያተኮሩ ነበሩ ለማለት ይቻላል።

## *6. የኢሕአዴግ መልሶ ማጥቃት*

### *6.1 የተቃዋሚ መሪዎች ወህኒ መወርወር*

ኢሕአዴግ በአብዛኛዎቹ ክልሎች ከፍተኛ ሽንፈት ሲገጥመው ዴሞክራሲያዊ የመምሰሉ ድራማ አክትሞ በመላ አገሪቱ ሁሉን ዐቀፍ የማጥቃት ዘመቻ ተጀመረ። በተለይ እስከ ስልፍ ባመሩትና ከረር ያሉ ተቃውሞዎች በታዩባቸው አካባቢዎች የፌዴራል ፖሊሱና የጦር ኃይሉ ከፍተኛ ጥቃት አኪያሂደው ነበር። ከነዚህ ብርቱ ጥቃት ከደረሱባቸው አካባቢዎች አንዱ አዲስ አበባ ሲሆን ሌሎችም አካባቢዎች ከጥቃቱ አላመለጡም። ለምሳሌ በሸካ መዠንገር አካባቢ ከምርጫውጋ በተያያዘ ሁኔታ በተፈጠረው የሕዝብ ቁጣ የእርስ

በእርስ ሁከት ተነሥቶ ሰላምና መረጋጋት የመፍጠር ኃላፊነት የነበረው የኢሕአዴግ አስተዳደር በስፍራው እያለ ብዙ ሕይወትና ንብረት ጠፍቷል። እንዲሁም በአዋሳ የኢሕአዴግ ታጣቂዎች የብዙ ንጹሐን ዜጎች ሕይወት የቀጠፈ ጥቃት አኪያሂደዋል። በወቅቱ ያልተዘገቡ ሌሎች ጥቃቶችም በበርካታ የአገሪቱ ክፍሎች ተኪያሂደዋል።

ኢሕአዴግ በዚህ ሁሉ ሳይረካ ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት ስትራቴጂ ነድፎ ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሕይወት ካጠፋና በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ካሰረ በኋላ፣ በርካታ የቅንጅት መሪዎችን በቁጥጥር ሥር አውሎ በዘር ማጥፋትና ሕገ መንግሥቱን በዐመፅ በመናድ ወንጀል እንዲከሰሱ አደረገ። ቅንጅትን ዘር ለማጥፋት ክስ ያበቃው በትግራይ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ቅስቀሳና ጥቃት ማኪያሂዱ ነው ተብሎ ነበር። በእርግጥም ቅንጅቶች በምርጫው ቀውስ ጊዜ የሰከነና የተስተካከለ የፖለቲካ አቅጣጫ መከተል አቅቷቸው አንዳንድ አላስፈላጊና መልሰው ራሳቸውን የሚጎዷቸው እርምጃዎች በግብታዊነት ወስደው ነበር። ለዚህም ሁለት ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። አንደኛው ቀደም ሲል የገለጽኩት ቅንጅት አዲስ አበባ ላይ ሰልፍ በጠራበት ወቅት በድሩ አደም *«ኢሕአዴጎች በመጡበት ይመለሱ»* ብሎ መናገሩ ሲሆን ሌላው ደግሞ የቅንጅት አመራር ሕዝቡ የትእምት ድርጅቶችን ምርት ከመጠቀም እንዲታቀብ ያስተላለፈው መመሪያ ነበር። እነዚህና ሌሎች ተመሳሳይ ቅስቀሳዎች ዘር ከማጥፋት ባይወዳደሩም በትግራይ ሕዝብ ሥነ-ልቦና ላይ ከፍተኛ ትጽዕኖ እንዳሳደሩ ቀደም ብዬ ገልጨዋለሁ። በእርግጥ በድሩ አደም ኢሕአዴጎች በመጡበት ይመለሱ አለ እንጂ ትግሬዎች በመጡበት ይመለሱ አላለም። ሆኖም ኢሕአዴጎች ወደ መጡበት ይመለሱ ሲል የትግራይ ሕዝብ ይሸከማቸው ከማለት ብዙ አይለይም። በሌላ በኩል፣ ኢሕአዴግም ይህን የቅንጅት አመራር አባባል አስቀድሞ ኢንተርሃምዌ መጣብህ ከሚለው መቀስቀሻው ጋራ አያይዞ ጉዳዩን ወደ ዘር ጥላቻ ለመለጠጥ ተጠቅሞበታል።

ሌላው ቅንጅት የተሳሳተው በትእምት በተመረቱ ምርቶች ላይ የተዓቀበ መሪያ ሲያስተላልፍ ነው። ይህ መመሪያ ከሲቪል ዐድማ ጋራ ተያይዞ እንደ ስልት ቢቀርብም ቅንጅት ከትግራይ ሕዝብጋ ይበልጥ እንዲራራቅ አደረገው እንጂ የፖለቲካ ትርፍ አላስገኘለትም። በዚህ ረገድ የቅንጅት አመራር መሠረታዊ ስሕተት ኢምንት የሆነው የትእምት ምርት በህወሓት/ኢሕአዴግ ኢኮኖሚ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል ብሎ መገመቱ ነው። ሁለተኛውና ይበልጥ ስሕተት የነበረው ደግሞ በትግራይ ሕዝብ ዕይታ የትእምት ድርጅቶች እንደሕዝብ ሀብት መቆጠራቸውን ቅንጅቶች አለመገንዘባቸው ነው። እንኳን በ1997 ዓ.ም. እና አሁንም ቢሆን በርካታ የትግራይ ተወላጆች የትእምትን ሀብት ሕዝቡ እንጂ የህወሓት አመራር እንደልብ የሚያዝበት መሆኑን አያውቅም። ይህን ዓይነት አመለካከት ያለውን ሕዝብ የትእምትን ምርቶች አትግዙ ማለት በትግራይ ባለቤትነት የሚመረተውን ምርት አትግዙ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር። ይህም በሕዝቡ እንዲሁም በጦር ኃይሉ፣ በፖሊሱና በደኅንነት ክፍሉ የነበሩትን የትግራይ ተወላጆች ያስቆጣ ነበር። ይህን በምርጫ 97 ቅንጅት በትግራይ ሕዝብ ላይ ያሳደረውን ሥነ-ልቦና በ2002 ዓ.ም. ምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የመቀሌ ነዋሪዎች የቅንጅትን ከፍተኛ አመራር ኢንጂኔር ግዛቸውን ይቅርታ እንዲጠይቁ አመልክተው ኢንጂኔሩ ይቅርታ ጠይቀዋል።

ከዚህ ሌላ፣ ቅንጅት ፍጹም የማይቆጣጠራቸው አባላቱ ነገሮችን እየለጠጡ በሕዝቡ መኻል መቃቃርን የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎች ያኪያሂዱ ነበር። ለምሳሌ አንዳንድ የትግራይ ተወላጆች ታክሲ ላይ ሲሳፈሩ፣ መንገድ ላይ ሲሄዱና በሌሎች አጋጣሚዎች ትንኮሳዎች ያጋጥሟቸው ነበር። ይህን የቅንጅት አኪያሄድ ህወሓት ይበልጥ ያስጮኸው ስለነበር በተለይ በትግራይ ተወላጆች ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤ ተፈጥሮ ነበር። ሁኔታው ይህን ቢመስልም ቅንጅት በፓርቲ ደረጃ ዘር የማጥፋት ወንጀል እንዳልፈጸመ ግን ግልጽ ነበር። ለዚህ

ማስረጃ የሚሆነውም የቅንጅት ደጋፊ ሰልፈኞች ብዙ የአዲስ አበባን አካባቢዎች በተቆጣጠሩበት ወቅት የትግራይን ተወላጆችን ለይተው ለመጨፍጨፍ አለመንቀሳቀሳቸው ነው። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የትግራይ ተወላጆች በሚበረክቱበት በጨርቆስ አካባቢ የአንድ የትግራይ ተወላጅ ንብረት በሰልፈኞች እንደተዘረፈና ቤቱም እንደተቃጠለ በተደጋጋሚ ቢያሳይም ይህ ድርጊት ከዘር ማጥፋት ወንጀል የሚቆጠር አልነበረም። በሩዋንዳ፣ በዩጎዝላቪያ፣ በኬንያ፣ ወዘተ.. የታዩት አንዱ ብሔር ሌላውን የመጨፍጨፍ ሁኔታ በኢትዮጵያ በምርጫ 97 ወቅት አልታየም። በአገራችን ፍትሕ የለም እንጂ፤ ቅንጅትን የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽሟል ብሎ መክሰሱ፤ ኢሕአዴግን ራሱን ባስጠየቀው ነበር። ተቻችሎና ተስማምቶ በኖረውና ለመኖር በሚፈልገው የኢትዮጵያ ሕዝብ መኻል የተቃዋሚዎችን ስሕተት እያጎላ ኢንተርሃምዌ መጣብህ ብሎ ማሸበር የጀመረው ኢሕአዴግ ነው።

የሆነው ሆኖ የቅንጅት አመራር አባላት በዘር ማጥፋትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በመናድ ተከሰው ለፍርድ ከቀረቡ በኋላ የተለያዩ ቅጣቶች ተበየኑባቸው። ሁኔታው ከተረጋጋና ኢሕአዴግ በትረ ሥልጣኑን በአስተማማኝ ሁኔታ እንደተቆጣጠረ ካረጋገጠ በኋላ፤ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ትርፍ ለማግኘት፤ የታሰሩትን የቅንጅት አመራር አባላት በይቅርታ አሰናበታቸው። ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎች የጠሩትን ሰልፍና ዐድማ ካከሸፈ በኋላ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን ያሰረው ከአጭር ጊዜ አኳያ ሊያጋጥመው የሚችለውን የሥልጣን መናጋት ለማስቀም ብቻ ሳይሆን፤ ከረዥም ጊዜ አኳያም የተቃዋሚዎችን ቅስም ለመስበር ነበር። ታስረው የነበሩት ተቃዋሚዎች ከእስር ሲፈቱ ቀደም ሲል የነበረው ትኩሳትና ብርቱ እንቅስቃሴ ቀዝቅዞ ከማግኘታቸውም በላይ፤ እስሩ በመኻላቸው ውዝግብ ፈጥሮ ነበርና ሞቅ ያለ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ሊቀጥሉ አልቻሉም። በዚህ መንገድ ኢሕአዴግ የአጭርና የረዥም ጊዜ ግቡን ለማሳካትና ሥልጣኑን ለማደላደል ቻለ።

## *6.2 ፓርላማው እንዳይናገር መሸበቡ*

ኢሕአዴግ በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ማግስት የወሰዳቸው እርምጃዎች በርካታ ሲሆኑ ከነዚህ አንዱ ሕዝቡ ከኢሕአዴግ የተለየ ድምጽ እንዳይሰማ ማድረግ ነበር። ለዚህም ገዥው ፓርቲ በአብላጫ የሚቆጣጠረው ምክር ቤት የሚያደርጋቸውን ክርክሮች ለሕዝቡ ተሟልተው እንዳይደርሱ የአሠራርና የሥነ-ምግባር አዋጅ አውጥቶ ነበር። አዋጁ *«በአጀንዳዎች አቀራረብ ቅደም ተከተልና ለውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜ በተመለከተ የመንግሥት ዋና ተጠሪ እና አፈጉባኤው በጋራ በመመካከር ይወስናሉ፤»*[19] በሚል የአንድ ተቃዋሚ ፓርቲ የፓርላማ አባል የንግግር ጊዜ ከአስራ ዐምስት ደቂቃ እንዳይበልጥ እንዲሁም በግለሰብ ደረጃ ሕዝብን የወከለ የፓርላማ አባል በአፈ ጉባኤው ችሮታ ለአንድ ደቂቃ ብቻ እንዲናገር ወስነው ነበር። የሚገርመው ኢሕአዴግ ይኸን አሠራር ያገኙት ከተለያዩ ዴሞክራሲን ከሚያራምዱ አገሮች ነው ማለቱ ነበር።

በአንድ አገር ኅብረ ፓርቲያዊ ሥርዓት ይኑር ሲባል በምርጫ ወቅት ብቻ ሳይሆን ዘወትር ፓርላማው ሕግ ለማርቀቅና ለማጽደቅ የሚያደርጋቸውን ክርክሮች አድምጦ የሚበጀውን ፖሊሲ ለመምረጥ እንዲችል ነው። ኢሕአዴግ በፓርላማ የተቀናቃኞቹን ንግግር በጊዜ የመገደብ አሠራር ሲያመጣ ግን ሕዝቡን አማራጭ ሐሳብ፣ ፖሊሲና መረጃ ከማግኘት እየገደበው እንደነበር ጥርጥር የለውም። ኢሕአዴግ የተቃዋሚዎች ንግግር እንዲገደብ ያደረኩት ስብሰባ እንዳይንዛዛ፣ ማሰሪያ እንዳይጠፋና ጊዜ እንዳይባክን ነው ይል ነበር።

---

[19] የተሻሻለው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሠራርና የአባላት የሥነ-ምግባር አዋጅ፣ *ነጋሪት ጋዜጣ፣ አሥራ አንደኛ ዓመት ቁጥር 60፣ አዋጅ ቁጥር 470/1998 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ መስከረም 26 ቀን 1998፤* አንቀጽ 12 ቁጥር 5፣ ገጽ 3254

አስቂኙ ነገር ግን ስብሰባ የሚንዛዛውና መቋጫ የሚያጣው ጠቅላይ ሚኒስትሩና ሌሎች የኢሕአዴግ ተወካዮች የፈለጋቸውን ጊዜ ወስደው ተረት እየደረደሩ በዙሪያ ጥምጥም አነጋገራቸው ተቃዋሚዎችን ሲያብጠለጥሉና ሲዘልፉ ሳይሆን ተቃዋሚዎች ገና አፋቸውን ሲከፍቱ መሆኑ ነው፡፡ ከሥለጠነ ፓርላማ የሚጠበቀው ከማንኛውም ወገን የሚቀርብ ሐሳብና ጥያቄ በሚገባ እንዲንሸራሸር በቂ ጊዜ ፈቅዶ ማስተናገድ ነው፡፡ ይኽን ግን አላለውምና ፓርላማው የኢሕአዴግ ማላገጫ ሆኖ ሊደመጡና ክብር ሊሰጣቸው የሚገባቸው የሕዝብ ተወካዮች ልጓም ተበጅቶላቸው የሕዝቡ መረጃ የማግኘት መብት ተገደበ፤ የፖለቲካ ምኅዳሩም ጠበበ፡፡

## *6.3 የሲቪል ማኅበረሰብ ነጻነት መነፈግ*

ኢሕአዴግ በምርጫ 97 ማግስት የወሰደው ሌላው አስከፊ እርምጃ የነበሩትን የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት ነጻነት በእጅጉ መግታቱ ነው፡፡ ይህን ለማድርግ የነበረውን የሲቭል ማኅበራት ሕግ *«አሻሽሎ»* አዲስ *«የበጎ አድራጎት ድርጅትና የማኅበራት አዋጅ»* ሕግ አጸደቀ፡፡ ይህን ሕግ ነጻነት ፈላጊ ዜጎች፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ ሲቪልና ዲፕሎማቲክ ማኅበረሰባት አጥብቀው ተቃውመውታል፡፡ የሁሉም ተቃውሞ ነጻነቱ የተጠበቀ ንቁ ሲቪል ማኅበረሰብ መኖሩ በዴሞክራሲ ግንባታ የማይተካ ሚና አለው በሚለው ሐሳብ ላይ ያጠነጠነ ነበር፡፡

ኢሕአዴግ ከምርጫ 97 በኋላ ያወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅትና የማኅበራት ሕግ ሲቪል ማኅበረሰቡ በፖለቲካዊና በሲቪል መብቶች መስክ ጉልሕ ተሳትፎ እንደይኖረው የሚያደርግ ነበር፡፡ ለዚህም በሰብአዊ መብት ነክ ጉዳዮች በተለይ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማራመድ፣ የብሔር ብሔረሰቦችን፣ የሴቶችን፣ የሃይማኖትን፣ የአካል ጉዳተኞችንና የሕፃናትን መብቶች በማረጋገጥ፣ በግጭት ማስወገድና በዕርቅ፣ በፍትሕና በሕግ አፈጻጸም በመከተል የተሰማሩ *«የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች»*[20] እንቅስቃሴያቸውን እንዲያቆሙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሕጉ በገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ያሉትን *«ብዙኃን ማኅበራት»*[21] በመንግሥት እየተደጎሙ በምርጫ እንዲሳተፉ ይፈቅዳል፡፡ አዋጁ *«ኢትዮጵያውያን ብዙኃን ማኅበራት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በምርጫ ሂደት በተለይም ትምህርታዊ ሴሚናሮችን በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በማዘጋጀት፣ የተወዳዳሪዎችን ፕሮግራም በማስረዳት፣ የምርጫ ሂደቶችን በመታዘብና ከምርጫ አስፈጻሚ አካላትጋ በመተባበር ረገድ በንቃት መሳተፍ ይችላሉ»*[22] ይላል፡፡

ከላይ እንደጠቀስኩት ኢሕአዴግ አዲስ ያጸደቀውን አዋጅ መሠረት በማድረግ ቀደም ሲል ከሞላ ጎደል ነጻ ሆነው ይንቀሳቀሱ የነበሩትን ሲቪል ማኅበረሰባት ካፈረሰና ከተቆጣጠረ በኋላ የራሱ የሆኑ *«ሲቪል ማኅበረሰባት»* ተጠናክረው እንዲቋቋሙ አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት የወጣት ማኅበር ወይም ሊግ፣ የሴቶች ማኅበር የሴቶች ሊግ፣ የገበሬዎች ማኅበር፣ የኢሕአዴግ ደጋፊ ነጋዴዎች ፎረም፣ ወዘተ… እየተባሉ በተግባር መንግሥት የሚቆጣጠራቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች *(Governmental and Non-Governmental*

---

20 *የበጎ አድራጎት ድርጅትና ማኅበራት አዋጅ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር 25፣ አዋጅ ቁጥር 621/4521፣ የካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣* አንቀጽ 2 ቁጥር 3፣ ገጽ 4522 *«የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጎ አድራጎት ድርጅት»* ወይም *«የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማኅበር»* ማለት ሁሉም አባላቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ፣ ከአስር ከመቶ በላይ ገቢ ከውጭ ምንጭ የሚያገኝና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማኅበር ነው፡፡

21 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 2 ቁጥር 5፣ ገጽ 4522 *«ብዙኃን ማኅበራት»* ማለት የሙያ፣ የሴቶች፣ የወጣትና ሌሎች ተመሳሳይ የኢትዮጵያ ማኅበራትን ያካትታል፡፡

22 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 57፣ ገጽ 4543

Organizations-GONGOs) ተፈልፍለዋል። እነዚህ ድርጅቶች በርካታ ጥቅማ ጥቅሞችን እያገኙ የመንግሥትንና የገዢውን ፓርቲ መመሪያ በኅብረተሰቡ ለማስፈጸምና የፖለቲካ ምኅዳሩን ለማጥበብ ከፍተኛ አሉታዊ ሚና ተጫውተዋል። እንዲሁም በአንጻሩ ለኅብረተሰቡ ጥሩ አስተዋፅኦ ያደርጉ የነበሩት ሲቪል ማኅበረሰባት ለምሳሌ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር፣ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ሕግ ባለሙያዎች ማኅበርና የነጋዴዎች ምክር ቤት በኢሕአዴግ አባላት ወይም ኢሕአዴግን አፍቃሪ በሆኑ ግለሰቦች ሙሉ ቁጥጥር ሥር ውለዋል።

ከዚህ ቀደም ብሎ በንጉሡ ጊዜና በደርግ የመጀመሪያ ዓመታት በኅብረተሰቡ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበሩትን የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርንና የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበርንም ኢሕአዴግ ተቆጣጠሯቸው ነበር። ኢሕአዴግ ይህን ሁሉ ያደርግ የነበረው ሲቪል ማኅበራት ነጻ ሆነው ከተደራጁ የመንግሥትን ግዙፍ መዋቅራዊ ጫና ሊቃወሙ እንደሚችሉ ከምርጫ 97 ዓ.ም. ተምሮ ስለነበር ነው።

## *6.4 የግል ፕሬሱ በቁጥጥር ሥር መዋል*

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የዴሞክራሲን መርሕ መሠረት በማድረግ የተቀረጸው የአገራችን ሕገ መንግሥት ዜጎች ሐሳባቸውን ያለምንም ገደብ መግለጽ እንደሚችሉ ይደነግጋል። ሐሳብን በነጻ ለመግለጽ ከሚያስችሉት መሣሪያዎች አንዱ ነጻ ፕሬስ እንደመሆኑ ሕገ መንግሥቱ ለፕሬሱ ልዩ ጥበቃ እንደሚያደርግ ይደነግጋል። በእርግጥም ዜጎች በመጠኑም ቢሆን ሐሳባቸውን ይገልጹባቸው ከነበሩበት አግባቦች አንዱ ደካማ ይባል የነበረው ነጻው ፕሬስ ነው። በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበረው ፕሬስ የገዢውን ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ ከማስተጋባት ያለፈ ሚና አልነበረውምና የግል ፕሬሱ ብቸኛው የሕዝብ ልሳን ሆኖ ለሕዝቡ የተሻለ መረጃ ጭላንጭል ያሳይ ስለነበር የተሟሟቀ ፖለቲካና ከፍተኛ ተወዳጅነት አትርፎ ነበር።

ኢሕአዴግ የግል ፕሬሱን፣ በተለይ የግል ጋዜጦችን፣ ቀለል ባለ ተጽዕኖ ሲያሠራቸው ቆይቶ ከምርጫ 97 በኋላ የግል ጋዜጣ ባለቤቶችን በማሰር ንብረታቸው እንዲወረስና ባለሙያዎቻቸውና ሠራተኞቻቸው እንዲበተኑ አደረገ። በወቅቱም ኢትዮጵያ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የፕሬስ ጠላቶች ተብለው ከሚፈረጁ አገሮች ተርታ ለመሰለፍ በቃች።

ኢሕአዴግ በምርጫ 97 ማግስት የግል ፕሬሱን ለዘለቄታው የሚቆጣጠርበትን ውጥን ሲሸርብ ቆይቶ በመጨረሻ ዐፋኝ የሆነ የፕሬስ ሕግ አወጣ። የፕሬስ ሕጉም ልክ በፓርላማ የነበሩት የተቃዋሚዎች ሐሳብ ሲገደብ እንደተባለው የበርካታ አገሮችን ልምድ መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው ተባለ። አዲሱ የፕሬስ ሕግ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ነበሩት። አንደኛው በፕሬስ ሠራተኞችና በኀታሚዎች ላይ የተጫነው ከባድ ቅጣት ሲሆን ሕጉን በመተላለፍ የስም ማጥፋት ክስ ከተመሠረተ እስከ አንድ መቶ ሺሕ ብር የሚደርስ የኅሊና ጉዳት ካሳ ሊበየን ከመቻሉም በላይ የግል ፕሬስ ባለቤቶችንም እስከ ሁለት መቶ ሺሕ ብር የሚቀጣ ነበር።[23] ቅጣቱ ማንኛውንም ጋዜጠኛና የመገናኛ ብዙኃን የሚያስበረግግና ራሱን ሳንሱር እንዲያደርግ የሚያስገድደው ነበር።

ሁለተኛው ችግር በ2001 ዓ.ምቱ *«የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ ነጻነት»* አዋጅ ደንጎቶችና የጸጥታ ክፍሎች ከፍርድ ቤት ዕውቅና ውጪ በመንግሥትና በገዢው ፓርቲ ላይ ጠንከር

[23] *የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አሥራ አራተኛ ዓመት፣ ቁጥር 64፣ ኅዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣* አንቀጽ 41 ቁጥር 2 ገጽ 4356 እና አንቀጽ 45 ቁጥር 1 ገጽ 4360

ያሉ አስተያየቶችን በሚሰነዝሩት ላይ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችላቸው አንቀጽ መደንገጉ ነው። በዐዋጁ፤ *«ዓቃቤ ሕግ ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሣ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገኛ ትእዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መጽሐፍ እንዲታገድ ትእዛዝ መስጠት ይችላል። ሆኖም ዓቃቤ ሕግ አንድን በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መጽሐፍ እንዲታገድ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔ በተሰጠ በ48 ሰዓት ውስጥ ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለበት። ፍርድ ቤቱ የእገዳ ማስታወቅያ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ የእገዳ እርምጃውን የሚያፀድቅ መሆን አለመሆኑ በውሳኔ ማሳወቅ አለበት።»*[24] የሚል አንቀጽ አካቶ ነበር። አንቀጹ ፍርድ ቤት የመወሰን ነጻነት ያለው ቢያስመስልም ሁሉም የመንግሥት አካላት በገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር በሆኑበት ሁኔታ ይህ ምንም ትርጉም አልነበረውም። ስለሆነም ሕጉን ተከትሎ በርካታ ጋዜጦኞች በፖሊስና በደኅንነት አባላት እየተጠሩ ማስፈራርያ ደርሶባቸው ነበር።

እያንዳንዱ በጋዜጣ የሚወጣው ጽሑፍ በደኅንነቶችና በጸጥታ ኃይሎች ሲመረመር በጸሐፊዎቹና በጋዜጣ ባለቤቶቹ ላይ ምን ዓይነት ችግር ይፈጥር እንደነበር ከበርካታ አብነቶች መገንዘብ ይቻላል። ሐቁን ጠንከር ብለው በሚገልጹ ጋዜጦች ላይ ብቻ ሳይሆን ልዝብ ትችት በሚያቀርቡትም ላይ በየጊዜው ወከባ ይደርስባቸው ነበር። የግል ጋዜጦችን በማሳተምና በነዚህ ጋዜጦች ላይ ሲጽፉ የነበሩ አንዳንድ ጋዜጠኞች በደረሰባቸው እንግልትና እስር አገር ጥለው ተሰደዋል፤ አንዳንዶቹም በወህኒ እየማቀቁ ይገኛሉ። ከነዚህ ጋዜጠኞች መኻል የሡርካለም አሳታሚዎቹ እስክንድር ነጋና በእስር ላይ የወለደችው ባለቤቱ ሡርካለም ሊጠቀሱ ይችላሉ። እስክንድር ከምርጫ 97 በኋላ ለአስራ ሰባት ወራት ከታሰረ በኋላ ተፈቶ የጋዜጠኛ ፈቃዱን ተቀምቶ ቆይቶ በ2003 ዓ.ም. እንደገና በሽብርተኝነት ተከሶ ወህኒ ወርዷል። በአጋጣሚ ከሞት ተረፈ እንጂ፤ የሪፖርተር ጋዜጣ ባለቤት አማረ አረጋዊ በጠራራ ፀሐይ ተደብድቧል። የአዲስ ነገር ጋዜጣ መዘጋትና የባለቤቶቹና የዓምደኞች መሰደድም ኢሕአዴግ ምን ያህል የፕሬስ ጠላት እንደሆነ ያመለክታል። እንዲህም የአገራችን ገና ያልተጠናከሩ ነጻ ጋዜጦች በሥርዓቱ ተጽዕኖ ተዘግተው ሕዝቡ የመንግሥትንና የድርጅትን ጋዜጦችና መጽሔቶች ብቻ እየተጋተ ይገኛል።

ኢሕአዴግ ከምርጫ 97 በኋላ የፖለቲካ ምኅዳሩን ለማጥበብ በፕሬሱ ላይ ብቻ ሳይሆን በኤሌክትሮኒክ ሚድያውም ላይ ጦርነት ከፍቶ ነበር። የሚያስገርመው ነገር ኢሕአዴግ ሐሳብን እንደ ጦር ወደሚፈራበት ደረጃ ወርዶ ልክ ደርግ ያደርግ እንደነበረው የአየር ሞገዶችን ማፈኑ *(Jamming)* ነው። ደርግ ህወሓትና ሻዕብያ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ያስተላልፏቸው የነበሩትን የሬድዮ ስርጭቶች በማፈን በተቃዋሚ ፓርቲዎች በህወሓትም ጭምር ይወገዝ ነበር። ኢሕአዴግ ከደርግ በባሰ ሁኔታ የውጭ ማለትም የአሜሪካንና የጀርመን ሬድዮዎችንም ጭምር እያፈነ ይገኛል። በኢንተርኔቱም እንዲሁ ገዢውን ፓርቲ የሚቃወሙ ድረ ገጾች ሲዘጉ ይታያ። በአጠቃላይ ለዴሞክራሲ ቆሚያለሁ፣ ሐሳብን በሐሳብ ማቸነፍ ይቻላል በሚለው መርሕ አምናለሁ የሚለው ኢሕአዴግ ይህን ኹሉ ሲያደርግ ምን ያህል እንደተሸነፈና የፖለቲካ ምኅዳሩን ለማጥበብ ቆርጦ እንደተነሣ መገንዘብ ይቻላል።

## *6.5 አሸባሪው የፀረ-ሽብር አዋጅ*

ኢሕአዴግ በራሱ መስፈርት የፈቀደውን የፖለቲካ ምኅዳር የበለጠ ለማጥበብ የፀረ-ሽብር አዋጅም አውጇል። የዚህ አዋጅ ዓላማ ዜጎችን አሸብሮ የኢሕአዴግን ሥልጣን ለማራዘም ስለነበር ሽብርተኝነት የሚለውን ቃል እጅግ የተለጠጠ ትርጉም በመስጠት፣ ሲፈልግ

---

[24] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 42 ቁጥር 4 /ሀ/፣ ገጽ 4357

ዜጎችን ሽብርተኞች ብሎ ፈርጆ በእስርና በሞት ሊቀጣቸው በሚያስችለው አግባብ እንደሚከተለው ገልጾታል፤

*«ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን የፖለቲካ፣ የሃይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግሥት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር፣ ኅብረተሰቡን ወይም የኅብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት ወይም የአገሪቱን መሠረታዊ ፖለቲካዊ፣ ሕገ መንግሥታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማኅበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይም ለማፍረስ፦*

*1/ ሰውን የገደለ ወይም በአካሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣*

*2/ የኅብረተሰቡን ወይም የኅብረተሰቡን ክፍል ደኅንነት ወይም ጤና ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ እንደሆነ፣*

*3/ እገታ ወይም ጠለፋ የፈጸመ እንደሆነ፣*

*4/ በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣*

*5/ በተፈጥሮ ሀብት፣ በአካባቢ፣ በታሪክ ወይም የባሕል ቅርስ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፣*

*6/ ማንኛውም የሕዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ሥር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይም ያበላሸ እንደሆነ፣ ወይም*

*7/ በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 6 ከተመለከቱት ድርጊቶች መካከል ማንኛውንም ለመፈጸም የዛተ እንደሆነ፣ ከ15 ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል»*[25] ይላል::

በአገራችን ለዝንት ዓለም የቆየው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በፀረ-ሽብር ሕጉ የተካተቱትን የወንጀል ድርጊት ፈጻሚዎች እንደሚቀጣ ግልጽ ሆኖ ሳለ፣ ኢሕአዴግ ይህን ተጨማሪ ሕግ ማውጣቱ በቁጥጥሩ ሥር ያሉትን የዓቃቤ ሕግና የፖሊስ ተቋማትን ተጠቅሞ ተቀናቃኞቹን ለማጥፋት ያለመ በመሆኑ በርካታ የሰብአዊ መብት ተማጓቾችና ዜጎች በጥብቅ ተቃውመውታል::

ሽብር ለሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉምም ዜጎች በሰላማዊ አግባብ ለመታገል የሚያስችላቸውን ምኅዳር አጥተው በሥርዓቱ ላይ እንዳይነሡ የሚያደርግም ነው:: የዛሬውን አይበለውና ኢሕአዴግ ደርግ የፖለቲካ ምኅዳሩን ዘግቶታል ብሎ ነፍጥ አንግቦ እንዳልተፋለመና የተመድን የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ እንዳልተቀበለ ሁሉ የሰላማዊን ትግል አማራጮች ሁሉ ጥርቅም ማድረጉን በፀረ-ሽብር ሕጉ አረጋግጧል:: የተመድ ሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ፤ *«የሰው ልጅ አምባገነንነትንና ጭቆናን ለመቃወም ዐመፅን እንደ መጨረሻ አማራጭ ለመጠቀም እንዳይገደድ ሰብአዊ መብቶችን በሕግ የበላይነት ማስጠበቁ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ»*[26] ሲል አምባገነኖች ሰብአዊ መብቶችን የማያከብሩ ከሆኑ ሕዝቡ ዐመፅን እንደአማራጭ ሊጠቀም እንደሚችል ቢደነግግም ኢሕአዴግ በሥርዓቱ ላይ የሚዝተውን ብቻ ሳይሆን ምንም ዓይነት ነቀፌታ የሚያሰማውን ሁሉ በሽብርተኝነት ከሶ እስከ ሞት ሊቀጣ እንደሚችል ደንግጓል::

---

[25] *የፀረ ሽብር አዋጅ፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አሥራ ዐምስተኛ ዓመት፣ ቁጥር 57፣ ነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣* አንቀጽ 3 ገጽ 4829

[26] The Universal Declaration of Human Rights. 1948, p. 1

ከዚህ ሌላ በፀረ ሽብርተኝነት ተጠርጥረው የሚከሰሱ ወገኖች ፍርድ ሳይሰጣቸው ለምርመራ ለኻያ ስምንት ቀናት፣ አስፈላጊ ከሆነም ለአራት ወራት፣ በቁጥጥር ሥር ሊውሉ እንደሚችሉ ሕጉ ይደነግግ ነበር። ይህን በተመለከተ የፀረ-ሽብር ሕጉ የሚከተለውን ይላል፤

*«አንቀጽ 19 ቁጥር 2፣ በዚህ አዋጅ የተመለከተ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸሙ ወይም እየፈጸመ ያለ ስለመሆኑ በሚገባ የሚጠረጥረውን ማንኛውንም ሰው ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ፖሊስ ለመያዝ ይችላል። ምርመራው ያልተጠናቀቀ እንደሆነ መርማሪው ፖሊስ ምርመራውን የሚፈጽምበት በቂ ጊዜ እንዲሰጠው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል።*

*አንቀጽ 20 ቁጥር 3/፣ በማረፊያ ቤት ለምርመራ ለማቆየት የሚሰጠው ጊዜ እያንዳንዱ ጊዜ ቢያንስ 28 ቀናት ይሆናል። ሆኖም በአጠቃላይ የሚሰጠው ጊዜ ከአራት ወራት መብለጥ የለበትም።»*[27]

ኢሕአዴግ እነዚህን አንቀጾች ተጠቅሞ ይቃወመኛል የሚለውን ወገን እያሰረና እያሰቃየ ይገኛል። ዐልፎ ዐልፎም ዓይኑ የገቡትን ለ28 ቀናት ወይም ለአራት ወራት ካሰረና ካሰቃየ በኋላ ቢፈታቸውም የሚደርስባቸው የሞራል ጉዳትና ውድቀት ቀላል አይደለም። የአንቀጹም ዋና ዓላማ ይኸው ተቃዋሚዎች በዚህ መንገድ ማንበርከክ ነው።

ከዚህ ሌላ ማንኛውም ዜጋ ሳያውቅ እንኳን ሽብርተኛ ተብሎ ከሙጠረጠር ሰውጋ ለኻያ አራት ሰዓታት ያህል አብሮ ከታየ በሽብርተኝት ሊከሰስ እንደሚችል የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ይገልጻሉ። ይህ ሕግ መለስ ብዙ ጊዜ እንዳለው ነጥብ እንኳን ሳይለወጥ ከምዕራባውያን ቢቀዳም የሚያሳዝነው የምዕራባውያኑ አጠቃላይ ዴሞክራሲያዊ ማዕቀፍ አብሮ ሳይቀዳ ቅጣቱ ብቻ መኮረጁ ነው። በአጠቃላይ ሕጉ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የጸደቀ ሳይሆን በፀረ-ሽብርተኝነት ስም መንግሥታዊ ሽብርን የሚያሰፍንና ዓለም ዐቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን የሚጻረር መሆኑ ግልጽ ነው።

## 7. የደነገጠው ጭንቅላት ተጨማሪ እርምጃዎች

### 7.1 ብሔሮችን ማፋጠጥ

በኢሕአዴግ ትንታኔ በምርጫ 97 መሠረቱን ያናጋው ቅንጅት የአማራ ትምክሕተኞች ወኪል ተብሎ ተፈርጆ ነበር። ኢሕአዴግ የአማራውን ሕዝብ ይወክላል ብሎ የሰየመው ብአዴን በምርጫው ክፉኛ ተዘርሮ እንኳንስ የአማራውን ሕዝብ ሊወክል ለራሱም መቆም አቅቶት ነበር። ኢሕአዴግ የጸጥታ ኃይሉን አሰማርቶ ተቃዋሚዎችን ባይበታትንለት ኖሮ ብአዴን እንደ ፓርቲ ጠንክሮ ለመቀጠልም እጅጉን በተቸገረ ነበር። ኢሕአዴግ የቅንጅትን መሪዎች ወሀኒ ከመወርወር ዐልፎ ቅንጅት መጣባችሁ፤ ሊውጣችሁ ነው፤ ሊያጠፋችሁ ነው፤ የሚለውን ማስፈራርያ እየተጠቀመ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች፣ በተለይ ከኦሮሞዎችና ከትግሬዎችጋ ሊያጋጨው ሞክሮ ነበር። ኢሕአዴግ ኦሕዴዶችን እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ በማንባር ቀደም ፀረ-ቅንጅት ፍልሚያ ለማሰለፍ ሞክሯል። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ከምርጫ 97 በፊት ኢሕአዴግ ኦሕዴድን የኦሮሚያ ዋና ከተማውን ከአዲስ አበባ /ፊንፊኔ/ ወደ ዝዋይ፣ ጅማና አዳማ እንዲለውጥ ይወተውተው ነበር። በመጨረሻም በቂ ጥናት ተደርጓል ተብሎ አዳማ የኦሮሚያ ከተማ እንድትሆን ተመረጠች። ኦሕዴዶች ይህን ውሳኔ በሁለት ምክንያቶች ከልብ አልተቀበሉትም ነበር። አንደኛ በኦሮሚያ መሬት ከተቆረቆረችው አዲስ አበባ መውጣታችን ተገቢ አይደለም

[27] ዝኒ ከማሁ፣ የፀረ ሽብር አዋጅ፣ ገጽ 4835

የሚለው ስሜታቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አብዛኛው አዲስ አበባ የተተከለው የመንግሥት ሠራተኞችን እግር አስነቅሎ መውጣቱ ከማኅበራዊና ከኢኮኖሚያዊ ትስስር አንጻር እጅግ ይጎዳናል የሚለው ነበር። ለማንኛውም ውሳኔውን ባይወዱትም አሕዴዶች ደረጃ በደረጃ ወደ አዳማ ለመዘዋወር ወስነው በብዙ ሚልዮን ብር ወጪ በአዳማ ከተማ ጽሕፈትና መኖሪያ ቤቶችና የስብሰባ አደራሾች ገንብተው ነበር። ለዚህ ግንባታ የወጣው ወጪ ቀላል ባይሆንም ብዙ የኦሮሚያ የመንግሥት ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ከለመዷቸው ትምህርት ቤቶች፣ የሥራ ቦታዎችና ማኅበራዊ መስተጋብሮች በመነቀላቸው የተከፈለው ዋጋ በገንዘብ ብቻ የሚሰላ አልነበረም።

ኢሕአዴግ በምርጫ 97 ከፍተኛ ሽንፈት ከደረሰበት በኋላ ከላይ የተጠቀሰውን ውሳኔውን በድንገት ሽሮ አሕዴድ እንደገና ዋና ከተማውን ከአዳማ ወደ አዲስ አበባ እንዲለውጥ ውሳኔ አስተላለፈ። ያሁሉ ገንዘብ ፈሶ በአዳማ አደራሹ፣ የሰማዕታት ሐውልቱ፣ ቤቱ ከተሠራና ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ከፈናቀሉ በኋላ እንደገና ቀኝ ኋላ ዙር ተብለው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። በዘመቻ መልክ ከአዲስ አበባ ወደ አዳማ የመሄዱንም ሆነ ከአዳማ ወደ አዲስ አበባ የመመለሱን ውሳኔ የኦሕዴድ አባላት መክረውበት ቢፈጸም ባልከፋ ነበር። ለማንኛውም የተደረገው ዝውውር የአገር ሀብትን ከማባከን፣ የሕዝቡን የተረጋጋ ኑሮ ከማወክና ሥነ-ልቦናውን ከመረበሽ ያለፈ ውጤት አልነበረውም።

ኢሕአዴግ ይህን ሁሉ ያደርግ የነበረው የአዲስ አበባ አስተዳደር ሙሉ በሙሉ ትምክሕተኞች ብሎ በሚፈርጃቸው በቅንጅቶች ቁጥጥር ሥር ስለገባ ይህን ሚዛን ለማዛባት ነበር። ቅንጅት የአዲስ አበባን አስተዳደር አልረከብም ብሎ ነገሩን በአጭር ቀጨው እንጂ አዲስ አበባን ቢረከብ ኑሮ በኦሕዴድ አማካይነት ብዙ ሤራዎች በተጎነጎኑበት ነበር። ምናልባትም የአዲስ አበባ ተጠሪነት ለሁለት ምክር ቤቶች ተከፍሎ ውዝግብ በተፈጠረም ነበር። ከሕግ አንጻር አዲስ አበባ በአንድ በኩል የፌዴራል መንግሥት ዋና ከተማ በመሆኗ ተጠሪነቷ ለፌዴራል መንግሥቱ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኦሮሚያ ዋና ከተማ በመሆኗ ተጠሪነቷ ለኦሮሚያ ነው በተባለም ነበር። ኢሕአዴግ እንዲህ ዓይነቱን ተንኮል ከመሸረቡ ሌላ አዲስ አበባ ውስጥ የተፈጠረውን የቅንጅት ተጽዕኖ ለመቋቋም በኦሮሞዎች ኃይል ለመጠቀም የአማራ ነፍጠኞችና ትምክሕተኞች ሊበሉህ ነው የሚል ቅስቀሳ ያኪያሂድ ነበር። ለማንኛውም ኢሕአዴግ ተቀበለውም አልተቀበለውም አብዛኛው የአማራ ሕዝብ ከኢሕአዴግ ይልቅ ቅንጅትን መርጦ ስለነበር ቅንጅት የበለጠ የአማራው ሕዝብ ውክልና አግኝቶ ነበር። ይህ ሆኖ ሳለ ቅንጅትን በትምክሕተኝነትና በነፍጠኝነት መክሰሱ በምርጫው የተሳተፈውን ሕዝብም ከበሬታ ማሳጣት ብቻ ሳይሆን ኦሮሞውንና አማራውን ማጋጨትም ነበር።

ቅንጅት የአዲስ አበባን መስተዳደር አልረከብም ካለ በኋላ የከተማው አስተዳደርና የከንቲባነቱ ሥልጣን የኦሮሞ ተወላጅ ለሆኑት ለብርሃኑ ደሬሳ ቢሰጥም የከተማይቱን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚከታተለው ኢሕአዴግ ነበር። ከአዳማ ተነቅሎ የገባው ኦሕዴድም ያን ያህል የጎላ ሚና አልነበረውም። ኢሕአዴግ አዲስ አበባን በተመረጠ ከንቲባ እንድትመራ አደርጋለሁ ብሎ ኩማ ደመቅሳ ከንቲባ ቢሆንም በአዲስ አበባ መስተዳደር ወሳኝ ተጽዕኖ የነበረው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነበር። ኦሕዴድና ኦሮሞዎች ቅንጅት ሥጋት በፈጠረበት ጊዜ ለኢሕአዴግ ቢደርሱለትም ቅንጅት ከተዳከመ በኋላ ግን እነእርሱ ራሳቸውም የሥጋት ምንጭ ተደርገው ሚናቸው እጅግ የተወሰነ ነበር። ሌላው ቀርቶ ኦሮሚያ በአዲስ አበባ ልዩ ጥቅም ይኖረዋል የሚለው በሕገ መንግሥቱ የሰፈረው አንቀጽ ለውለታቸው ሲባል እንኳን ተፈጻሚነት አላገኘም ነበር። የኦሕዴድ አመራር እንኳንስ እጅግ ውስብስብ በሆነውና ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች በአብላጫ ባሉበት በአዲስ አበባ ቀርቶ በኦሮሚያ ክልልም የመወሰን ሥልጣን አልነበረውም። እ.አ.አ. በ2007 ዓ.ም. በተደረገው

አጠቃላይ የሕዝብ ቆጠራ በአዲስ አበባ 2,739,551 /*ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሠላሳ ዘጠኝ ሺሕ ዐምስተ መቶ ኀምሳ አንድ*/ ሕዝብ ይኖር ነበር። ከአጠቃላዩ ኗሪ ኦሮሞው 534,487 /*ዐምስት መቶ ሠላሳ አራት ሺሕ አራት መቶ ሰማንያ ሰባት*/ ወይም 19.51 ከመቶ ነበር።[28] በዚህ ስሌት የኦሮሞው ብዛት ዝቅተኛ *(minority)* ስለነበር አስተዳደሩ በምርጫ ቢቋቋምና ሁሉም የብሔሩ አባላት ድምጻቸውን ቢሰጡ ኦሕዴድ ሥልጣኑን ሊቆጣጠር የሚችልበት ሁኔታ አልነበረም። በነገራችን ላይ የከተማው ነዋሪ በምርጫ ወቅት ድምጹን የሚሰጠው በብሔር ላይ ተመሥርቶ ስላይደለ ከተሜውን እንደ ገጠሬው በብሔር መከፋፈል አይቻልም። ኢሕአዴግ በከተሞች፣ በተለይ ደግሞ በአዲስ አበባ፣ ብሔሮች የጎሪጥ እንዲተያዩ የማድረግ ፖለቲካው ያልተሳካለትም በዚሁ ምክንያት ነበር።

## *7.2 ኢሕአዴግ የአፈጻጸም ችግሮቼን አስወግጃለሁ ማለቱ*

ኢሕአዴግ በምርጫ 97 ማግስት በችኮላ ከወሰዳቸው እርምጃዎችና ከሰጣቸው መግለጫዎች አንዱ የግብር ቅነሳ አዋጅ ነበር። ሆኖም ግብር የተቀነሰው ለጊዜያዊ ፖለቲካዊ ፍጆታ እንጂ ሕዝቡና ነጋዴው በግብር ተጎድቷል ከሚል እምነት የተነሣ አልነበረም። ከጊዜ በኋላ እንደታየው ከምርጫ 97 በፊትም ይሁን በኋላ የኢሕአዴግ ትክክለኛ እምነት ኢትዮጵያ በግብር አሰባሰብ ረገድ፣ በተለይ ከጎረቤት አገሮችጋ ስትወዳደር እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች የሚል ነበር። ኢሕአዴግ የሚፈልገው ግብርን በተጠናከረ መንገድ መሰብሰብ ሆኖ ሳለ በምርጫው ማግስት የግብር ክፍያ ደረጃዎችን ማሻሻሉ በግብር ጫና ያኮረፈውን ነጋዴ ለማባበል እንደነበር ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል።

ከዚህ በተጨማሪም ኢሕአዴግ በርካታ ሕዝቡን የሚያስከፉና በአስተዳደር ዙሪያ የተፈጸሙ ስሕተቶችን በአብዛኛው በበታች አባላቶቹና መዋቅሮቹ ተፈጽመዋል ቢልም እንዳሉ አምኗል። *«አለባብሰው ቢያርሱ በዐረም ይመለሱ»* እንዲሉ ኢሕአዴግ ለጊዜው የሕዝቡን ቀልብ ለመሳብ ተሳስቻለሁ ይበል እንጂ የበላይ ባለሥልጣናቱን ተጠያቂ ለማድረግና የችግሩ መሠረታዊ ምንጭ ምን እንደሆነ ለመግለጽ ግን ፈቃደኛ አልነበረም። ኢሕአዴግ ችግሬ መሠረታዊ የፖሊሲና የመዋቅር ሳይሆን የአፈጻጸም ነው ሲል የሚያታልለው ራሱን ብቻ ነበር። በምርጫው ወቅት መሬት በመንግሥት ሹማምንትና በካድሬዎች የሚዘረፍና የሚከበርበት እንጂ ሕዝቡ የሚጠቀምበት አይደለም የሚል መሠረታዊ ጥያቄ ተነሥቶ ነበር። የተፈጠረው የፌዴራል ሥርዓትም የሕዝብ ውሳኔ ሰጭነት የተረጋገጠበት ሳይሆን ኢሕአዴግ እንዳሻው የሚያሽከረክረው እንደሆነም ተገልጾ ነበር። እንዲሁም ግብርና መር የሚለው የልማት ስትራቴጂ ዘላቂ ልማትን እያረጋገጠ እንዳልሆነና ለአገራችን ችግር መፍትሔ እንዳልሆነ ተጠቁሞ ነበር። ከተሸነፈም በኋላ ኢሕአዴግ እነዚህን የፖሊሲ ችግሮች ለመቀበል ዝግጁ አልነበረም። ከዚህ ሌላ ኢሕአዴግ ዴሞክራሲን ማፈኑ፣ ሰብአዊ መብቶችን መርገጡ፣ የሕግ የበላይነትን ያለማስከበሩ፣ በሙስናና በብልሹ አስተዳደር መዘፈቁ፣ በግልጽ ተነግሮት ነበር። ጳፉ ይህን መቀበል ከሥልጣን መወገድን ያስከትልብኛል በሚል ፍራቻ ችግሬ የአፈጻጸም እንጂ የፖሊሲ አይደለም በሚለው አቋሙ ጸንቶ ነበር።

ኢሕአዴግ በምርጫው ማግስት ሕዝቡ መቶ በመቶ መርጦኛል ባለው በትግራይ እንኳን ከፍተኛ ትችት ደርሶበት ነበር። በወቅቱ፣ መለስ የተወሰኑ ነጋዴዎችን መቀሌ ላይ አግኝቶ ምሬታቸውን ሲገልጹለት፣ መለስ *«እኛ ልጆቻችሁ ነን፣ ብናጠፋም መገሠጽና መመከር አለብን እንጂ መገለል የለብንም፤ ልጅ ሲያጠፋ አባት ይመክረዋል እንጂ አይርቀውም፤»* ብሎ በሥነ-ልቦናቸው ተጫውቷል። ብሶተኞቹም *«ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው እሳት*

[28] Central Statistical Agency (CSA) of Ethiopia. 2007.

ሆነባት እንዳትተወው ልጅ ሆነባት» የሚለውን አባባል አውስተው ተለዩት። በወቅቱ የትግራይ ነጋዴዎች ያነሷቸው ችግሮች ከአፈጻጸም ሳይሆን ከመሠረታዊ የፖሊሲ ችግር የመነጩ ነበሩ። ለምሳሌ የትእምት በሞኖፖል ተቆጣጥሮ የዝቅተኛ ነጋዴዎችን የንግድ እንቅስቃሴ መግደል ግልጽ የፖሊሲ ጥያቄ ነበር።

ኢሕአዴግ ጊዜ ለመግዛት የአፈጻጸም ችግሮቼን ለወደፊት አስተካክላለሁ፤ ይህን ካላደረኩም አሁን የመዘዛችሁትን ብጫ ካርድ ወደ ቀይ ትለውጡታላችኹ እያለ የማታለል እንቅስቃሴውን ቀጥሎ ነበር። ለነገሩ ኢሕአዴግ አልታይ ብሎት እንጂ በምርጫ 97 ሕዝቡ ያሳያው ካርድ፣ በራሱ እምነት፣ ብጫ ሳይሆን ደማቅ ቀይ ነበር። የሕዝቡ ፍላጎት ኢሕአዴግን አስወግዶ ሌሎች ፓርቲዎችን መሞከር ነበር። ሕዝቡ በኢሕአዴግ ላይ የነበረው ምሬትም በአፈጻጸምና በፖሊሲ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በመሠረታዊ የአወቃቀርና የባሕርይ ጉዳዮች ላይም ያተኮረ ነበር። ኢሕአዴግ በምንም መንገድ የብዙኃን ፓርቲዎችን ሥርዓት፣ የፍትሕ ሥርዓትን ነጻነት፣ የመንግሥት አካላት አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠሩበትን አሠራርና ነጻ ሲቪል ማኅበረሰብን የማይቀበል የአንድ ፓርቲን ፈላጭ ቆራጭነት የሚያራምድ እንደነበር ማንም ያውቃል። አስራ አራት ዓመት ያህል አገርን ሲመራ በየዓመቱ የሚዘረዘሩት ችግሮች እጅግ እየተበራከቱና እየባሱ ሊፈቱ ወደማይችሉበት ደረጃ መድረሳቸው ምንጫቸው የመሠረታዊ ፖሊሲና ተቋም መሆኑን በግልጽ ያመለክት ነበር። በመሆኑም ኢሕአዴግ በየአጋጣሚው ያገሪቱ ችግሮች እንደሚፈታ ቃል ቢገባም ክስተቶችን እንጂ ምንጩን ስለማይነካ ሊፈታው አልቻለም።

## *8. የ2002 ምርጫና የኢሕአዴግ ፍጹም የአንድ ፓርቲ አገዛዝ*

### *8.1 ቅድመ ምርጫ ሁኔታዎች*

ኢሕአዴግ በምርጫ 97 ክፉኛ ተደናግጦ የወሰዳቸውን የፖለቲካ እርምጃዎች በመተግበር ሥራ ላይ ተጠምዶ በ1999 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ የአካባቢ ምርጫ ለማኪያሄድ ሲወስን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ እንዲኪያሄድ መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ከገዢው ፓርቲ ጋ ለመነጋገር ሐሳብ ቢያቀርቡም ኢሕአዴግ ይህን ሐሳብ ወደ ጎን ትቶ የጀመረውን ዝግጅት ቀጠለ። ይባስ ብሎም በወረዳና በቀበሌዎች የምክር ቤት አባላት ይሆናሉ ያላቸውን ቁጥር እጅግ ከፍ አድርጎ ተቃዋሚዎችን ከጨዋታ ውጭ ለማድረግ ተጨማሪ ስልት ቀየሰ። በዚህም መሠረት በአገሪቱ ጠቅላላ የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ከሦስት ሚልዮን ዐምስት መቶ ሺሕ በላይ እንዲሆኑ ሲወስን፣ ተወዳዳሪዎቹም በጣም ትናንሽና የተበታተኑ በመሆናቸው ለኢሕአዴግ ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት።

ተቃዋሚዎች በርካታ ዕጩ ተወዳዳሪዎች አለማቅረባቸው የራሳቸው ድክመት ነው ሊባል ቢችልም የአገራችንን ሁኔታ በሚገባ ለሚያውቅ ሰው በተለይ በገጠር አካባቢ የኢሕአዴግ ተቃዋሚ ሆኖ መገኘት ምን ያህል አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያቅተውም። የተቃዋሚ ፓርቲ አባል መሆን እርዳታ የሚያስከለክል፤ መሬትና ማዳበሪያ የማግኘት ዕድልን የሚያጠብ፤ በገዢው ፓርቲ ዓይነ ቁራኛ የሚያስገባ፣ ለእስርና ለእንግልት የሚዳርግ ሆኖ እንኳንስ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ለመሆን ደጋፊም ለመሆን የሚከጅል አልነበረም። በአንጻሩ ኢሕአዴግ እንደማንኛውም ያላደገ አገር ገዢ ፓርቲ አባላቱን በጥቅማ ጥቅም እየደለለ ሰፊ እንቅስቃሴውን በተሟሟሊ ሁኔታ ያኪያሂድ ነበር። ኢሕአዴግ አባላት ለማግበስበሱ ምክንያት የሆነውም በ97ቱ ምርጫ ለሽንፈት የበቃሁት አገሪቱን በስፋት የሚሸፍን የአባል ብዛት ስላልነበረኝ ነው የሚለው ግምገማው ነበር። በዚህ መሠረት

ኢሕአዴግ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ አባላትን ለመመልመል የሚቆጣጠራቸውን የመንግሥት ግምጃ ቤትን፣ መሬትን፣ እርዳታን፣ የተለያዩ የንግድ ፈቃዶችን፣ የመንግሥት ሥራ ቅጥርንና የጸጥታ ተቋማትን ተጠቅሞ ነበር። በመሆኑም፣ ተምሮ ሥራ ለማግኘትና በመንግሥት ሥራ እድገትና ነጻ የትምህርት ዕድል ለማግኘት የሚሯሯጠው፣ መሬቱን እንዳይነጠቅ፣ በንግድ እንቅስቃሴው ጫና እንዳይደርስበት፣ የእርዳታ እህል እንዳይከለከል፣ በጸጥታ ተቋማት ወከባ እንዳይደርስበት፣ የሚሠጋው ሁሉ የኢሕአዴግ አባል ለመሆን ማመልከቻ በሰልፍ የሚያስገባበት ሁኔታ ተፈጠረ። እንዲህም፣ ኢሕአዴግ በገጠርም ሆነ በከተማ የፈለገውን ያህል አባል ለማሰባሰብ ቻለ፣ ተቃዋሚቹም አባል ለማግኘት ተቸገሩ።

ኢሕአዴግ በገፍ በመለመለው አባል ድጋፍ ምርጫውን ለማሸነፍ በተስተካከለበት ሁኔታ መሸነፋቸው ሳይታለም የተፈታው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫው ላለመሳተፍ ወሰኑ። ተቃዋሚዎች ከምርጫው በፊት እውነተኛ ፉክክር እንዲኖር የጨዋታው ሜዳ እንዲመቻች የጠየቁትም እንዲህ ዓይነት ሁኔታ እንዳይፈጠር ነበር። ተቃዋሚዎች በተዛባው ምርጫ አንሳተፍም ሲሉ በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ መሠረት በሁለት ተከታታይ ምርጫዎች ሳይሆን፣ በአንድ ምርጫ አንሳተፍም ሊሉ እንደሚችሉ የተቀመጠላቸውን መብት በመጠ ቀም ነበር። በዚህ የአካባቢ ምርጫ እንደ ኢዴፓ ከመሳሰሉት አንድ ሁለት ፓርቲዎች በስተቀር የተሳተፈ ሌላ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ አልነበረም። ኢዴፓም ቢሆን ከዚህ ምርጫ ያገኘው የፖለቲካ ጥቅም ሳይሆን ኢሕአዴግ እንደ አጃቢ አድርጎት ተወዳድሬ አሸንፊያለሁ ለማለት ማገልገሉ ነበር። ኢሕአዴግ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መንገድ የአካባቢ ምርጫ እንዲከናወን አድርጎ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ መቀመጫዎችን ከተቆጣጠረ በኋላ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የፓርቲና የመንግሥት መዋቅሩን ፍጹም ተቆጣጠረ። ይህ አኪያሄዱ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ቀድሞ ከነበረው ይበልጥ እንዲከፋ አደረገው። በእያንዳንዱ የወረዳና የቀበሌ መስተዳደር መቶ በመቶ የአንድ ፓርቲ አባላት መሰባሰባቸው ከእነርሱ ውጪ የሆነን አስተሳሰብና እንቅስቃሴ ያለምሕረት ለመምታት አስቻላቸው።

የ2002 ዓ.ም. የክልልና አገር ዐቀፍ ምርጫ ሊኪያሄድ ቅድመ ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ በሥጋት የተዋጠው ኢሕአዴግ ተጨማሪ መመሪያዎችን ለካድሬዎቹና ለአባላቱ ሰጥቶ ነበር:: ይህ በ2002 ዓ.ም. መስከረምና ጥቅምት «አዲስ ራዕይ» በተባለው የኢሕአዴግ ልሳን ላይ የታተመው ስትራቴጂ በአገር ዐቀፉና በክልላዊው ምርጫ ተቃዋሚዎች እንዳች ወንበር እንዳያገኙ ለማድረግ ያለመ ነበር። በእርግጥ ገዢው ፓርቲ የሚወዳደሩትን ተቃዋሚዎች በሁሉም የምርጫ ጣብያዎች ለማሸነፍ ቢሞክር ኃጢአት አልነበረም። ኃጢአቱ ይህን መመሪያው ለማስፈጸም አባላቱና ካድሬዎቹ ማድረግ አለባቸው ያላቸው ኢ-ዴሞክራሲያዊ ተግባራት ነበሩ። ከነዚህ በመጽሔት ከሰፈሩ የአፈጻጸም አቅጣጫዎች መኻል ኢሕአዴግ በምርጫው በከፍተኛ ደረጃ ይገዳደረኛል ያለውን የ«መድረክ»ን ስም ለማጥፋት ያስተላለፈው መመሪያ ነበር:: መድረክ ከጠላትነት ዐልፎ «የጥፋት ኃይል» ተብሎ ተፈርጆ መመሪያው ለእያንዳንዱ የመድረክ አባል ድርጅት ሲመነዘር በኦሮሚያ ለመወዳደር የሚዘጋጁትን ኦፌዴንና ኦሕኮን ጠባቦችና ከነፍጠኛ ጋ አብረው የኦሮሞውን ጥቅም እንደሚጻረሩ፣ በአማራው ክልልና በተቀሩት የአገሪቱ ክፍሎች የሚወዳደረውን አንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲን ነፍጠኞች፣ ትምክሕተኞችና የኢሠፓ ቅሪቶች እንደተሰባሰቡበት፣ በትግራይ ሲንቀሳቀስ የነበረውን ዓረናን ደግሞ የትግራይ ሕዝብ መሠረታዊ ጠላቶች ከሆኑት ከቅንጅትና ከኢሠፓ ቅሪቶች ጋራ እንደሚተባበር አድርጎ ሁሉም ተቃዋሚዎች ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ይንቀሳቀስ ነበር።

ኢሕአዴግ መድረክን ብቻ ሳይሆን በምርጫው ተሳታፊ የነበሩትን ፓርቲዎች ሁሉ በኪራይ ሰብሳቢነት ወይም አግባብ የሌለው ትርፍ በማሰባሰብ ሊከሳቸው ዐቅዶ ነበር:: ይህን በተመለከተም ለአባላቱ ባሰራጨው የስትራቴጂ ጽሑፍ፣ «በኢትዮጵያ ያሉት ተቃዋሚ

*ኃይሎች ሁሉ በኪራይ ሰብሳቢነት ዙሪያ የሚታዩ ቢሆኑም የየራሳቸው የተለያየ ባሕሪ እንዳላቸው የማይካድ ነው። አንዳንዶቹ በጠባብነት ዙሪያ ሲሽከረከሩ ሌሎቹ በትምክሕተኝነት ዙሪያ የሚሽከረከሩ ናቸው። ጥቂቶቹ ለሕጋዊና ሰላማዊ ትግል ተገዥ ለመሆን ቆርጠው የተነሡ የሚመስሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ለዓመጽና ነውጥ የቋመጡ የተቀሩት ደግሞ እንደነገሩ ሁኔታ ካንዱ ወደ ሌላው ሊሸጋገሩ የሚችሉ ናቸው። ይህን ስትራቴጂ በምንቀይስበት ወቅት መነሻ የምናደርገው የዓመጽና የብጥብጥ አቅጣጫ የሚከተሉትን ነው። ይህን የምናደርግበት ምክንያትም ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ብዙዎቹ ፓርቲዎች ለሕግና ለሰላም ተገዥ እንሆናለን ብለው ቃል ቢገቡም በምርጫው ወቅት የሚደቀኑ ፈተናዎችን ሁሉ በተግባር አልፈው በቃላቸው የሚጸኑ ለመሆናቸው ተጨባጭ ተግባራዊ ማረጋገጫ ገና ስላልተሟላ ነው»*[29] ይላል። በመቀጠልም ተቃዋሚዎች ለዐመጽ እንደተነሡ በማረጋገጥ፤ *«በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ወንበር ማግኘት በማይችሉበትና ሥልጣን መያዝ የሁሉም የግል ብልጽግናቸው ማጠንጠኛ ባደረጉበት ሁኔታ ያላቸው አማራጭ ምርጫው ተአማኒነት እንዳያጣ ማድረግ ነው። ይህን በተመለከተ በአፍሪካም ሆነ በሌሎች አገሮች በተደጋጋሚ የተሠራበት አማራጭ ነውና ይህን ይከተላሉ። አማራጩ ምርጫው ተጭበረበረ ብሎ ሰፊ ግርግር በመፍጠር በሥልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ ማስወገድ ነው»*[30] ይላል።

ኢሕአዴግ በምርጫው ለመሳተፍ የወሰኑትን ተቃዋሚዎች ዐመጸኛ ካደረገ በኋላ ምርጫውን ለመቆጣጠር መከተል ስላለበት አቅጣጫም ሲዘረዝር ምርጫው ዜጎች በነጻነት የሚሳተፉበት መሆኑ ቀርቶ ዜጎች አንድ ለፀምስት ተደራጅተው የሚሳተፉበት ሆነ። በዚህ መሠረት፤ *«…የምርጫ ሰራዊትን በመገንባት የምርጫ ግቦቻችን የማሳካት ጉዳይም በመሠረቱ ከዚሁ የተለየ አይደለም።… የምርጫውን የሂሳብ ስሌት በማየት ይህ በተግባር ምን ማለት እንደሆነ መገመት ይቻላል። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ከ18 ዓመት በታች በመሆኑ የመራጩ ቁጥር ከ30 ሚልዮን በላይ ሊሆን እንደማይችል ይገመታል። ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 4 ሚልዮን የድርጅት አባላችን ነው። እያንደንዱ አባል በቀላሉ ሊቀርባቸውና ሊያሳምናቸው የሚችል ቢያንስ 4 ወዳጆችና ዘመዶች አሉት ብንል እነዚህ ተደምረው 20 ሚልዮን ይሆናሉ። በነዚህ ብቻ ቢያንስ 2/3ኛው ድምጽ ማግኘት ይቻላል። ከዚህ አልፎም በአባላችን ዙሪያ የተሰባሰበው 20 ሚልዮን ሕዝብ ቀሪው 10 ሚልዮን ሕዝብ ከተቻለ የኢሕአዴግን ግቦች በሙሉ እንዲደግፍ ካልሆነ በነጻና ዴሞክራሲያዊ ውድድር ማዕቀፍ እንዲታጠርና ዓመጽን እንዲቃወም ለማድረግ ለእያንዳንዱ ሰው ሁለት ሁለት ዘማች ቢመደብለት ሊገኝ የሚችለውን ውጤት መገመት አያዳግትም»*[31] ይላል።

በመቀጠልም የተቃዋሚ መሪዎችን ለመቅጣት፤ *«በሁለተኛ ደረጃ የሚታየው ሕገ ወጦችን በሕግ ፊት አቅርቦ ማስቀጣት ነው። እዚህ ላይም ወሳኝ የሚሆነው በየአካባቢው ያለው ተላላኪያቸውን መቅጣት አይደለም። ወሳኝ የሚሆነው ቁልፍ መሪዎችና አንቀሳቃሾች በወንጀላቸው ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታ መፍጠር ነው»*[32] ይልና ይህን ለማሳካት ደግሞ፤ *«ተቃዋሚዎች በግልጽም ሆነ በስውር የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ በቅርብ ተከታትለን ማስረጃ መያዝ አለብን። በተቻለ መጠን ሰነዶችን ለማግኘት መሞከር፣ ድርጊቶችን በቪድዮና በድምጽ ለመቅረጽ ጥረት ማድረግ አለብን። ይህ የተሟላና አስተማማኝ መረጃ የማግኘት ማስረጃ የማሰባሰብ ሥራ ቀጥሎ ላለው ሥራ ሁሉ የላቀ ድርሻ ስላለው በብቃትና ባለማቋረጥ ሊፈጸም የሚገባው ነው»*[33] ይላል። ቀጥሎም፤ *«በአገሪቱ ጠቅላላ የሚሠሩትን ሥራ ለበላይ አካል በአፋጣኝ እንዲደርሰው በማድረግ የበላይ አካል ሁኔታዎችንና*

---

[29] የ2002 የምርጫ ስትራቴጂያችን፣ *«አዲስ ራዕይ»*፣ መስከረም-ጥቅምት 2002፣ 2ኛ ዓመት፣ ቅጽ 3፣ ቁጥር 1፣ ገጽ 14

[30] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 15

[31] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 21

[32] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 26

[33] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 27

*ማስረጃዎችን አመዛዝኖ በምርጫው ሂደትም ሆነ ማጠናቀቅያ ላይ የማያዳግም ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድበት ሁኔታ መፍጠር ይቻላል።»*[34] በማለት ኢሕአዴግ የምርጫ ስትራቴጂውን ያጠቃልላል። ኢሕአዴግ በ2002 ምርጫ ቅደመ ዝግጅት ይህን ሰነድ ለካድሬዎቹና ለአባላቱ ማሰራጨቱ ምርጫውን ፍጹም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለማሸነፍ ቆርጦ መነሣቱን ያመለክት ነበር። ኢሕአዴግ የመድረክንና የእያንዳንዱ አባል ድርጅቱን ስም ለማጉደፍ የቀየሰው ስልት ሸፍጥን መሠረት ያደረገ፣ ከፖለቲካ ልዩነቶች ይልቅ የሕዝቡን ሥነ-ልቦና በፍርሀትና በጥላቻ በመስለብ ላይ ተመሥርቶ ድጋፍ ለማግኘት ያለመ፣ በአጠቃላይ በማንኛውም መንገድ ሥልጣንን ለመቆጣጠር የሚያስችለው ነበር።

መድረክ የኢሠፓ ቅሪት ነው የሚለውን የኢሕአዴግ አገላለጽ ጠንቀቅ ብለን ብንመለከተው እንኳን ከመድረክ ይልቅ በኢሕአዴግ፣ በአመራሩም ጭምር፣ የተሰገሰጉት የኢሠፓና የኢሠፓኮ አባላት ቁጥር ይበልጥ ነበር። ለነገሩ በአሁኑ ጊዜ ኢሠፓ በኢትዮጵያ ፖለቲካ አደጋ አይደለምና መድረክንም ራሱንም በዚህ ሊወነጅል አይገባም። በዚህ አጋጣሚ ከ1983 ዓ.ም. በኋላ ባሉት ሁለት ሦስት ዓመታት ኢሠፓ አገራዊ አደጋ እንደማይፈጥር ተረጋግጦ አባላቱ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ሕገ መንግሥቱ መብት እንደሰጣቸው ማስታወሱ ጠቃሚ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ በዜጎች ፖለቲካዊ ስብእና ላይ ጉዳት ማድረስ ሕገ መንግሥቱን መጻረር ነው። ኢሠፓ ዐፈናን፣ የዴሞክራሲያዊ መብቶች መጣስን፣ የሰብአዊ መብቶች መረገጥን፣ የሚያመለክት ከሆነ ያለጥርጥር በወቅቱ የተሰጠው የኢሠፓ ስያሜ የሚስማማው ለመድረክ ሳይሆን ለኢሕአዴግ ለራሱ ነበር።

ጠባብነትና ትምክሕተኝነትም ከተቃዋሚዎች ይልቅ ኢሕአዴግን የሚገልጹ ባሕርይዎች ናቸው። ኢሕአዴግ በየጊዜው አባል ድርጅቱ በሆነው በአሕዴድ ላይ ያደርግ የነበረው ግምገማ ጠባብነቱን የሚያጋልጥ ነበር። በህወሓት ውስጥም ጠባብነት ተከሰተ መባሉ አልቀረም። በተመሳሳይ ሁኔታ ብአዴኖች በአማራ በትምክሕተኝነት ዝንባሌ ዘወትር ይከሰሱ ነበር። በአጭሩ ኢሕአዴግ የነዚህ ሁለት አስከፊ አስተሳሰቦችን ቅይጥ ተሸክሞ የሚሄድ ድርጅት እንደሆነ እንቅስቃሴው ሁሉ ይመሰክራል። ጠባብነት ማለት ለተወለዱበት ብሔር ብሔረሰብ ቅድሚያ በመስጠት አገራዊ ጥቅምን ማሳነስ ነው ከተባለ እያንዳንዱ የኢሕአዴግ አባል ድርጅት ከአገራዊ ራዕይ እጅግ የራቀ ነውና ጠባብነት የሚለው ስያሜ ይስማማዋል። ኢሕአዴግ የሚቃወሙትን ድርጅቶች ጠላት የሚል ስም ቢሰጣቸውም ተቃዋሚዎች፣ በተለይም መድረክ፣ ኢሕአዴግን ከኢትዮጵያ እንደመነጨ የአገርን ጥቅም እንደማያስጠብቅ አምባገነን ኃይል ያዩታል እንጂ ጠላት አይሉትም። መድረክ ኢሕአዴግን ጠላት ቢያደርገው ኖሮ የሚከተለው ስትራቴጂም የመጠፋፋት *(Zero Sum Game)* እንጂ የፉክክር አይሆንም ነበር። ያም ሆነ ይህ ኢሕአዴግ የሚጫወተው የመጠፋፋት ፖለቲካ ከአስራ ዘጠነኛውና ከኻያኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሳይላቀቅ ሥልጣኑን ለማጠናከር እንደወሰነ ያሳያል።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህን የኢሕአዴግን ዝግጅት ያለ ምንም ኀፍረት በልሳኑ ያመለከተውን የፖለቲካ ምኅዳሩን የማጥበብ አቅጣጫ ካዩ በኋላ ሁኔታው እጅግ አስቻጋሪ እንደሚሆን ተገንዝበው ምርጫው ከመኪያሄዱ በፊት አሁንም ከገዢው ፓርቲ ጋራ ለመደራደር አበክረው ጠየቁ። ለድርድሩ ከሁሉም በላይ በርትቶ የተንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ነበር። መድረክ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በኢትዮጵያ ነጻ፣ ፍትሐዊና ተአመኒነት ያለው ምርጫ እንዲኪሄድ መደራደር እንደሚፈልግ ገልጾ ገንቢ ሚና ሊኖራቸው ይችላሉ ያላቸውን የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላትም ሊያሰባስብ

---

[34] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 28

ሞክሯል። ሆኖም ገዢው ፓርቲ የመድረክን ፍላጎት በሚገባ ተገንዝቦ ነበርና እንቅስቃሴውን ለማክሸፍ ተዘጋጀ።

ኢሕአዴግ ከምዕራባውያን ዲፕሎማቶች ይቀርብለት የነበረው ከተቃዋሚዎችጋ የመደራደር ጥያቄ እየበረታበት ሲሄድ በደፈናው አልደራደርም ከማለት ይልቅ እሺ እደራደራለሁ ብሎ ነገሩን ለማበላሸት መንቀሳቀስ ጀመረ። በዚህ መሠረት ከእንግሊዝ አምባሳደርና ከኤምባሲው ባለሥልጣናትጋ በመነጋገር የድርድሩን ይዘትና አኪያሄድ በተመለከተ ከተወያየ በኋላ የወቅቱ የእንግሊዝ አምባሳደር የነበሩት እና የፖለቲካ ኃላፊያቸው ጋቢን ኩክ ከመድረክ መሪዎችጋ ለመነጋገር ኢሊምፒያ አጠገብ ከሚገኘው *«ፊኒክስ ሬስቶራንት»* ቀጠሮ ያዙ። በቀጠሮው ቀን፤ የእንግሊዝ ኤምባሲው ባለሥልጣናት፣ ከእንግሊዝ አገር የመጡ እንግዶችን አስከትለው መጡ። በዚህ አጋጣሚ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ከተቃዋሚዎች ጋራ ለመደራደር እንደተስማሙና የድርድሩ አጀንዳም በምርጫ ሥነ-ምግባርና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩር ገልጸውልን ለመነሻ የህንድን፣ የደቡብ አፍሪካንና የጋናን የሥነ ምግባር ኮዶች ጠቅሰውልን የሁሉንም ሞዴሎች ቅጅ ከሰጡን በኋላ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ምርጫ የጋናው እንደሆነ ጠቆሙን። ድርድሩ የሚኪያሄደው ከመድረክ ጋራ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተቃዋሚዎችምጋ እንደሆነ ገለጹልን። ከዚያም ወዲያው መልስ እንድንሰጣቸው ፈለጉ። እኛም ጉዳዩን ሳንመክርበት መልስ እንደማንሰጣቸው አስታወቀናቸው በጥቂት ቀናት ውስጥ መልሳችንን እንደምናሳውቃቸው ነግረናቸው ተለያየን።

ከእንግሊዝ ኤምባሲ ባለሥልጣናት የሰማነውን ለመድረክ ሥራ አስፈጻሚ ካቀረብን በኋላ በጉዳዩ ዙሪያ ሰፊ ውይይት አኪያሂደን አቋማችን በእንግሊዝ ኤምባሲ በኩል እንዲተላለፍልን በጽሑፍ አቀረብን። በዚህ ጽሑፍ መድረክ በአጽንዖት ያነሣው ጉዳይ የድርድሩ እምብርት የምርጫው ሥነ-ምግባር ኮድ ሳይሆን የፖለቲካ ምኅዳሩ የሚመለከት መሆኑን ነበር። በተለይ በተቃዋሚዎች ላይ ይደርስ የነበረው ወከባና ጫና እንዲወገድ ተገቢ ያልናቸውን የድርድር ርእሶች ለይተን፤ 1ኛ/ የዴሞክራሲ መብቶች፣ በተለይ የመናገር፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቶች መከበር፣ 2ኛ/ የሰብአዊ መብቶች መከበር፣ በተለይ ደኅንነቶች፣ የኢሕአዴግ ካድሬዎችና የጸጥታ ኃይሎች ያለአግባብ በአባሎቻችን ላይ የሚያደርሱትን እስር፣ ድብደባና ጥቃት እንዲያቆሙ፣ 3ኛ/ የሕግ የበላይነት መከበርን፣ 4ኛ/ ለተቃዋሚዎች ስለሚደረገው የፋይናንስ ድጋፍ መዛባትን፣ 5ኛ/ የመንግሥት ሚድያ ፍትሐዊ አጠቃቀምን፣ አቀረብን። በነዚህ ርእሶች ዙሪያ ድርድር እንዲኪያሄድ ከጠየቅን በኋላ እንደማሳረጊያ፤ በምርጫ ኮዱና በሌሎች ምርጫ ነክ ሰነዶች ላይ እንደምንደራደርም ገለጽን።

ፍላጎታችን ለኢሕአዴግ አመራር ከተላለፈ በኋላ ኢሕአዴግ ያቀረብነውን የመደራደሪያ አጀንዳ እንደማይቀበለውና የፖለቲካ ምኅዳሩ ጉዳይ በምርጫ ኮዱ አጀንዳ ተካቶ ሊታይ እንደሚችል ተገልጾልን ድርድሩ የሚኪያሄደው ከመድረክጋ ብቻ ሳይሆን ኢሕአዴግ ጥሪ ከሚያደርግላቸው ከሌሎች ፓርቲዎችምጋ እንደሆነም ተነገረን። እንደኛ አመለካከት ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ እንዳይደረግ ዋነኛው ማነቆ ፖለቲካዊ ምኅዳሩ እንጂ የምርጫ ሥነ-ምግባር ኮዱ አልነበረምና ስለምኅዳሩ ለመደራደር ካልቻልን ጉዳዩ ፋይዳ የለውም ብለን ያቀረብናቸው ጥያቄዎች ትኩረት እንዲሰጣቸው አጥብቀን ተማጸንን። ሌሎች ፓርቲዎች ይጋበዙ መባሉም ተገቢ እንዳልሆነ ገለጽን። መድረክ ለድርድሩ ይጠራሉ የተባሉት ፓርቲዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ በሚገባ ያውቅ ነበር። ለምሳሌ ኢዴፓ በፓርላማ በቆየበት ጊዜና ከዚያም በኋላ በሦስተኛ ጎራ የመሰለፉን አቋምና ከኢሕአዴግጋ የነበረውን ጥብቅ ቁርኝት እናውቅ ነበር። ቅንጅትም የዋናውን ድርጅት ስም ተሸክሞ ቅንጅት ዳግም እንዳያንሰራራ በኢሕአዴግ መልካም ፈቃድ የተፈጠረ መሆኑንም እናውቅ ነበር። የአቶ መስፍን ሽፈራው ፓርቲም ሌላ መስካሪ ሳያሻው ኢሕአዴግ ራሱ የቤተሰብ ድርጅት

እንደሆነና ምንም ፋይዳ እንደሌለው ከመሰከረለት በኋላ በቁጥጥሩ ሥር አውሎት ነበር። ከሞላ ጎደል ነጻነቱን በማስጠበቅ የተሻለው ድርጅት መኢአድ ነበር። መኢአድም ቢሆን በጊዜው እንደኢሕአዴግ ጌጥ እየተሰለፈ እንደነበር ጥርጣሬ ነበረን። በመሆኑም ከመኢአድ በስተቀር ከሌሎቹ ከኢሕአዴግ ጎን ከተሰለፉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችጋ አብረን ተቀምጠን መደራደሩ ፋይዳ እንደሌለው ተገንዝበን ነበር።

ይህን አቋማችንን አገናኝ ለነበሩት የእንግሊዝ ዲፕሎማቶች በተደጋጋሚ ብናስታውቃቸውም ሁሉንም ነገር በግንባር ቀርባችሁ ተናገሩ የሚል ጫና ስላሳደሩብን ጥሪያቸውን አክብረን በድርድሩ መክፈቻ ስብሰባ ተገኝተን ያለንን አቋም ግልጽ አደረግን። እንደገመትነውም ኢሕአዴግ ሁል ጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ በዋናው አጀንዳ ከመነጋገር ይልቅ ሌሎች ፓርቲዎች በስብሰባው ቢሳተፉ ምንድን ነው ችግሩ የሚለውን አጀንዳ መዞ አውጥቶ ከጋበዛቸው ፓርቲዎች ጋራ ሊያጋጨን ከመሞከሩም በላይ የፖለቲካ ምኅዳርን የተመለከተም ይሁን ሌላ ጥያቄ ካላችሁ በተለየ መድረክ እንነጋገርበት አለን። ኢሕአዴግ አስቀድመን በምርጫ ሥነ-ምግባር ኮዱ እንነጋገር ሲል በመነሻነት እንድንነጋገርባቸው የተሰጡንን የተለያዩ አገሮች የምርጫ ሥነ-ምግባር ኮዶች ረቂቅ እንኳን አብረን እንድንወያይባቸው ዕድል ሳይሰጠን ራሱ የመረጠውን የጋናውን የምርጫ ኮድ ወደ አማርኛ ተርጉሞ እንድንወያይበት አሰራጨ። ይህ አኪያሄድ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና በፓርቲዎች የምዝገባ አዋጅ መሠረት ሁላችንም ከኢሕአዴግ እኩል ነን በምንለው ፓርቲዎች ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። በተለይ መድረክ የኢሕአዴግ አኪያሄድ የሸፍጥና የማጭበርበር ሆኖ ስላገኘው በስብሰባው አልሳተፍም ብሎ ወጣ። ለስብሰባው ከመድረክ ተወክለው ከሄዱት መኻል ከዘጠኝ ዓመት በፊት መቀሌ ላይ መለስን እያጭበረበርክ ነው ያሉትና ስብሰባውን ጥለው የወጡት አረጋሽ አዳነና አውዓሎም ወልዱ ነበሩና አሁንም ሌሎች የመድረክ አባላት ያስተጋቡትን ደግፈው ወጡ። የያኔው ስልቱ ይሠራልኛል ብሎ የገመተው ኢሕአዴግ *«ይኸውላችሁ እንደልማዳቸው ስብሰባውን ረግጠው ወጡ»* በማለት መድረክን ለማጥላላት ሞክሮ ነበር። በበኩላችን ኢሕአዴግ ጉዳዩን ረጋ ብሎ እንዲያየውና ተደራድረን እንድንሠራ አበክረን ጠየቅን። ሆኖም ከዲፕሎማቶች ይሁንታ በማግኘቱና ከመድረክ በስተቀር አራቱ ፓርቲዎች ከኢሕአዴግጋ ለመደራደር በመወሰናቸው ኢሕአዴግ መጀመሪያውኑ በቀረጸው አጀንዳ ገፋበት። ከጅምሩ በወቅቱ የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ የነበረውን መድረክን አግልሎ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋራ እየተደራደርኩ ነው ማለቱ፣ ኢሕአዴግ የተደራደረው *«ከራሱ ጥላ»* ጋራ ነበር ለማለት ያስችላል።

የኢሕአዴግ ፍላጎት አገራችን ውስጥ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ እንዲኪያሄድ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ መፍጠር ሳይሆን የፖለቲካ ምኅዳሩን ጥርቅም አድርጎ መዝጋት እንደሆነ በሚገባ ተገንዝበን ነበር። ኢሕአዴግ ባቀናጀው ድርድር የተሳተፉትን የአራት ፓርቲዎች ይሁንታ ካገኘ በኋላ በምርጫ ቦርድ አማካይነት የተቀሩት ፓርቲዎች በስምምነቱ ላይ እንዲፈርሙለት ጥሪ አደረገ። ጥሪው በምርጫ ቦርድ ይተላለፍ እንጂ አወያይና አጀንዳ አቅራቢ ሆነው የቀረቡት ኢሕአዴግና ተባባሪዎቹ ነበሩ። ስብሰባው ተጠርቶ ውይይት ከመኪያሄዱ በፊት የመድረክ ተወካዮች የዚሁ የሁሉም ፓርቲዎች ስብሰባ አስተባባሪና መሪ ማን እንደሆነ ለማወቅ ጥያቄ አቅርበው ኢሕአዴግ ፓርቲዎች ጠርቶ ለማወያየትና ውሳኔ ለማስተላለፍ ሕግ እንደማይፈቅድለት አስገነዘቡ። የምርጫ ሥነ-ምግባር ኮድ የመቅረጽና የማወያየት ሕጋዊ መብት ያለው የምርጫ ቦርድ ብቻ ነበር። ሆኖም ምርጫ ቦርዱ በወቅቱ መድረክ ላነሣው ጥያቄ የሰጠው መልስም፣ *«ምርጫ ቦርድ ማንኛውም ፓርቲ ስብሰባ እንዲጠራለት ከጠየቀ ስብሰባ ይጠራል። ኢሕአዴግ ይህ ስብሰባ እንዲጠራለት ስለጠየቀም የፓርቲዎቹ ስብሰባ ተጠርቷል፣»* የሚል ነበር። ስብሰባው ከተከናወነ በኋላም ከመድረክ በስተቀር እያንዳንዱ ፓርቲ የተላለፉትን ውሳኔዎች መቀበሉን በፊርማው አረጋገጠ። የሚገርመው ነገር በምርጫ ቦርድና በሕግ ፊት ኢሕአዴግና ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች